JIMMA UNIVERSITY
ጅማ ዩኒቨርሲቲ

# የጅማ ዩኒቨርሲቲ የ2010 በጀት

# 1ኛ ሩብ ዓመት ሪፖርት

## (ዝግጅት ምዕራፍ)

**ጅማ ዩኒቨርሲቲ ፕላንና ፕሮግራም ዳይሬክቶሬት**

**ቢሮ ስቁ** +251-471 11 2207 ጅማ www.ju.edu.et

**ሞባይል** +251 931 99 5050 planjimma@gmail.com

## ማውጫ


| | |
|---|---|
| ማውጫ | 2 |
| የሠንጠረዥ ዝርዝር | 3 |
| ክፍል አንድ   መግቢያ | 4 |
| ክፍል ሁለት አጠቃላይ አሃዛዊ መረጃ | 6 |
| ፕሮግራም አንድ- የስራ አመራርና መልካም አስተዳደር | 10 |
| ዓላማ 1.1. የሰው ኃብት ልማትና ተቋማዊ አመራርን ማሻሻል | 10 |
| ዓላማ 1.2. መልካም አስተዳደርን ማሻሻልና ማስፈን | 12 |
| ዓላማ 1.3. የገቢ ማመንጫ ዘርፎችንና የፋይናንስ አስተደዳርን ማጎልበት | 15 |
| ፕሮግራም ሁለት. የአካዳሚክ ልዕቀት | 17 |
| ዓላማ 2.1. የከፍተኛ ትምህርትን ተደራሽነትና ፍትሐዊነት ለማሳደግ የተከናወኑ ስራዎች | 17 |
| ዓላማ 2.2. የከፍተኛ ትምህርት ጥራትና አግባብነትን ለማሻሻል የተከናወኑ ስራዎች | 19 |
| ዓላማ 2.3. ኢንተርፕረነራል ትምህርትና የስራ ፈጠራ ክህሎትን ማሳደግ | 22 |
| ፕሮግራም 3. ጥናት ምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር | 23 |
| ዓላማ 3.1. ደረጃውን የጠበቀ ምርምር፣ ፈጠራና ግኝትን የሚያበረታታ ምቹ ሁኔታ መገንባት | 23 |
| ዓላማ 3.2. ፈጠራና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማስፋፋት | 24 |
| ፕሮግራም 4. ማህበረሰብ አገልግሎትና አሳታፊነት ልዕቀት | 25 |
| ዓላማ 4.1. በማህበረሰብ አቀፍ ትምህርት የማህበረሰቡን አገልግሎት ማጠናከር | 25 |
| ዓላማ 4.2. ዘመናዊ/ New age/ የህክምና ማዕከል መገንባት | 28 |
| ዓላማ 4.3. ዘለቄታዊ የአካባቢ ጥበቃን ማሳደግ | 28 |
| የዓለማቀፋዊነትና ተቋማዊ ትብብር ትኩረት መስክ | 29 |
| ዓላማ 5.1. ዓለማቀፋዊ ተወዳዳሪ ትምህርትና የምርምር መስኮችን ማበልፀግ | 29 |
| ዓላማ 5.2. ዓለማቀፍ ደረጃ የሚያሟሉ መምህራንና ተማሪዎችን መሳብና ስራ ላይ ማቆየት | 29 |
| ዓላማ 5.3. በምርምርና በትምህርት ዓለማቀፋዊ ትብብርን መመስረት/ ማጠናከር | 30 |
| ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች | 32 |

## የሠንጠረዥ ዝርዝር

ሠንጠረዥ 1. ስራ ላይ ያሉ ኢትዮጵያዊ መምህራን በትምህርት ደረጃ ........ 6
ሠንጠረዥ 2. ስራ ላይ ያሉ ኢትዮጵያዊ መምህራን በአካዳሚክ ደረጃ ........ 6
ሠንጠረዥ 3. ትምህርት ላይ ያሉ ኢትዮጵያዊ መምህራን ........ 7
ሠንጠረዥ 4. አዲስ የተቀጠሩ ኢትዮጵያዊ መምህራን ........ 7
ሠንጠረዥ 5. ስራ ላይ ያሉ የውጭ አገር መምህራን በትምህርትና ፆታ ........ 7
ሠንጠረዥ 6. የተማሪዎች ቁጥር በባንድ ........ 8
ሠንጠረዥ 7. አስተዳደርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች፣ እና ጤና ባለሙያዎች ........ 8
ሠንጠረዥ 8. አዲስ የተቀጠሩ፣ በዝውውር የመጡ፣ የተሰናበቱ የመንግሥት ሠራተኞች ........ 9
ሠንጠረዥ 9. ፋሲሊቲ ዝርዝር ........ 9
ሠንጠረዥ 10. የሰው ኃብት ልማት ልማትና ተቋማዊ አመራርን ማሻሻል ........ 10
ሠንጠረዥ 11. መልካም አስተዳደርን ማሻሻልና ማስፈን ........ 12
ሠንጠረዥ 12 .የተለያዩ የገቢ ምንጮችን ማፈላለግና ማሳደግ ........ 15
ሠንጠረዥ 13. የተማሪዎች ቁጥር ........ 17
ሠንጠረዥ 14. የከፍተኛ ትምህርት ጥራትና አግባብነትን ለማሻሻል የተከናወኑ ስራዎች ........ 20
ሠንጠረዥ 15. ጥናትና ምርምርና የቴክኖሎጂ ሽግግር ........ 23
ሠንጠረዥ 16 ማህበረሰብ አገልግሎት ........ 25
ሠንጠረዥ 17 የዩኒቨርሲቲው ህክምና ማዕከል ........ 28
ሠንጠረዥ 18 ዓለማቀፋዊ የምርምር መስኮች ........ 29
ሠንጠረዥ 19 በምርምርና በትምህርት ዓለማቀፋዊ ትብብርን ለመመስረት/ ለማጠናከር የተከናወኑ ስራዎች ........ 29
ሠንጠረዥ 20 ፕሮጄክቶችና የምርምር ማዕከላትና ኢንስቲትዩቶች ውጤቶች ........ 30

## ክፍል አንድ   መግቢያ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 63/1999 እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 22 ቀን 1999 ዓም በወቅቱ የግብርና ኮሌጅና የጤና ሳይንስ ኢንስቲተዩት ተብለው የሚጠሩ ሁለት ተቋማት በመዋሃድ የተቋቋመ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ነው፡፡ ዛሬ በአገሪቱ ካሉ አንጋፋና በተለይ በማህበረሰብ አቀፍ ትምህርት ፍልስፍናው ፈር-ቀዳጅና መሪ የሆነው ጅማ ዩኒቨርሲቲ “We Are in The Community” በሚለው መርህ የታወቀ ተቋም ሲሆን ከምስረታው ጀምሮ በስልጠና፣ በምርምርና በማህበረሰብ አገልግሎት ዘርፍ በርካታ ድሎችን ያስመዘገበና በትምህርት አሰጣጥ ጥረቱ ለአምስት ተከታታይ ዓመታት በኢትዮጵያ አንደኛ የወጣ ብቸኛ ተቋም ነው፡፡

ተቋሙ በምስረታው ወቅት በጥቂት የጤና፣ ህክምናና ግብርና መስኮች በአብዛኛው ዲፕሎማ መርሃ-ግብሮችን በማስተማር ላይ ተወስኖ የነበረ ሲሆን ይህ ሁኔታ ዛሬ በአስገራሚና ፈጣን ለውጥ ተቀይሮ በዚህ ዓመት በድምሩ በ236 የትምህርት ፕሮግራሞች ማለትም በ62 የቅድመ-ምረቃ፣ በ139 ሁለተኛ ዲግሪና በ35 ሶስተኛ ዲግሪ ፕሮግራሞች 40587 ተማሪዎች ተቀብሎ ያስተምራል፡፡ አምስት ካምፓሶች ያሉት ጅማ ዩኒቨርሲቲ በአጠቃላይ 7761 ሰራተኞች ያሉት ሲሆን ከዚህ መካከል 6016 የአስተዳደርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችና 1745 ኢትዮጵያዊ መምህራኖችን የያዘ ግዙፍ ተቋም ነው፡፡

ዋናው ካምፓስ ውስጥ የዩኒቨርሲቲዉ የበላይ አመራር፤ ማዕከል ቢሮዎች፣ ሦስት ኮሌጆችና የተቋሙ መማሪያ ሆስፒታል የሚገኙ ሲሆን ከዋናው ግቢ በ4 ኪሜ ርቀት ላይ የሚገኘው የግብርናና እንስሳት ህክምና ኮሌጅ ስምንት ትምህርት ክፍሎች ያሉት ካምፓስ ነው፡፡ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ኪቶ ፉርዲሳ ካምፓስም ከዋናዉ ግቢ በ6 ኪሜ ርቆ የሚገኝ ሲሆን ከዋናው ግቢ አጥርና መንገድ ባሻገር በስተደቡብ የሚገኘው የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ ካምፓስ 4 የትምህርት ክፍሎች ይዟል፡፡ ከጅማ ከተማ 42 ኪሜ ርቆ የሚገኘው የአጋሮ ካምፓስ በግንባታ ላይ ሲሆን ይህም አምስተኛው ካምፓስ ነው፡፡

በአገሪቱ እጅግ ልዩ በሆኑ የትምህርት ፕሮግራሞች በተለይም በባዮሜዲካል ኢንጂነሪንግና ጥርስ ህክምና ትምህርት ዘርፎች ፈር ቀዳጅ የሆነው ጅማ ዩኒቨርሲቲ የላቀ ትምህርት ባህልን በመገንባትና መሰረታዊ ችግሮችን መፍታት የሚያስችል ምርምሮች በማካሄድ ዓለማቀፋዊነትን በማስፋፋትና መላሽ ሰጪ አገልግሎቶች በመስጠት በርካታ ስራዎችን እያከናወነ ነው፡፡ አገራችንን ከድህነት አረንቋ ለመታደግና መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ ለማሰለፍ በሠው ኃይል አቅም ግንባታ ዘርፍ አያሌ ሚና በመጫወት ላይ ያለው ጅማ ዩኒቨርሲቲ መሠረታዊ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ የትኩረት አቅጣጫዎች ላይ ተመርኩዞ የተቀናጀ፣ ቀልጣፋና ስትራቴጂካዊ ስልቶችን ማስተግበር የሚያስችል ዓመታዊ ዕቅድ በማውጣት በርካታ ስራዎች በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ የዩኒቨርሲቲያችን ዋነኛ ተልዕኮ የሆኑትን መማር/ማስተማር፤ ምርምርና የህብረተሰብ አገልግሎት ተልዕኮዎች ለማሳካት ጥረት እየተደረገ ነው፡ ፡በተመሳሳይ ማህበረሰባችን የራሱን ችግሮች በራሱ እንዲፈታ ለማስቻል፣ የኢንቬስትመንት አቅማችንን ለመገንባትና ከባለድርሻዎቻችን ጋር እኩል ተጠቃሚ የሚያደርጉ ትስስሮችን በመፍጠር ራዕያችንን ዕውን ለማድረግ ርብርብ እየተደረገ ሲሆን በዚህም አዳዲስ ዕውቀትና ክህሎት ማንጨት የሚያስችሉ አመቺ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል፤ ለአገሪቱ አንገብጋቢ ችግሮች አዎንታዊ ለውጥ ማምጣት በሚያስችሉ የትኩረት መስኮች ግንባር ቀደም ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል፡፡

ይህ ዝግጅት ምዕራፍ ሪፖርት በአውቶሜትድ የውጤት ተኮር ስርዓት የማዘጋጀትና ሪፖርት የማቅረብ ሥራ እየተጠናቀቀ ባለበት በአሁኑ ወቅት በተለምዷዊ የወረቀት አሰራር የሩብ ዓመቱ ሪፖርት እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርቧል፡፡ ይህም ዩኒቨርሲቲው ስትራጂክ ዕቅዱን ለማሳካት እያደረገ ያለውን ጥረት የሚያሳይና የፕሮግራም በጀቲንግ አሰራርን መሰረት በማድረግ የቀረበ ሲሆን በተለይ ተቋሙ በስትራቲጂክ ዕቅድ ዘመኑ ያስቀመጣቸውን አምስት የትኩረት አቅጣጫዎች (የልህቀት ምሶሶዎች) ከግብ ለማድረስ በሚያስችሉ ዋና ዋና ፕሮግራሞች ስር የተከናወኑ ዝርዝር ስራዎችን ያሳያል፡፡

**ራዕይ**

በመማር/ ማስተማር፤ በምርምርና በማህበረሰብ አገልግሎት በ2025 እ.ኤ.አ. ከአፍሪካ ቀዳሚና በዓለም ታዋቂ ዩኒቨርሲቲ ሆኖ ማየት

**መሪ ቃል Motto**

"We Are in the Community" በማህበረሰቡ ውስጥ ነን

**ተልዕኮ**

የዩኒቨርሲቲው ፍስልስፍና በሆነው በማህበረሰብ አቀፍ ትምህርት፣ ስልጠናና የአካባቢውን፣ የአገሪቱንና ዓለማቀፉን ማህበረሰብ በማሳተፍ ብሔራዊና ዓለማቀፋዊ ብቃት ያላቸውን ምሁራንን የማፍራትና ጥራት ያለውና ችግር ፈቺ ምርምር ማከናወን

**ጅማ ዩኒቨርሲቲ**

በማህበረሰብ አቀፍ ትምህርት በአገሪቱ ፈር ቀዳጅና በትምህርት አሰጣጥ ጥረቱ ለአምስት ተከታታይ ዓመታት በኢትዮጵያ አንደኛ የወጣ ብቸኛ ተቋም

ጅማ ዩኒቨርሲቲ በሁለተኛው ስትራተጂክ ዕቅድ ዘመኑ በአምስት ዓበይት የትኩረት መስኮች የሚከተሉትን ስትራተጂያዊ ግቦች ለማሳከት ርብርብ በማድረግ ላይ ነው

1. **በአካዳሚክ ልዕቀት የትኩረት መስክ:** የላቀ ትምህርት ባህልን በመገንባት ምሁራዊ ብቃትና ሙያ ያላቸውን ምሩቃን እንገነባለን፤ በታላላቅ ድርጅቶች ውስጥ የመቀጠር ዕድላቸውን እናሰፋለን
2. **የምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ልዕቀት ትኩረት መስክ:** የአገሪቷንና ዓለማቀፍ ችግሮችን መፍታት የሚችናል ከፍተኛ ደረጃ ያላቸውን ምርምሮች እናካሂዳለን
3. **ማህበረሰብ አገልግሎትና አሳታፊነት ትኩረት መስክ:** ፈጠራንና መላሽ ሰጪ አገልግሎቶችን በማበርከት ማህበረሰቡ የራሱን ችግር በራሱ እንዲፈታ እናበቃለን
4. **በዓለማቀፋዊነትና ተቋማዊ ትብብር ትኩረት መስክ:** ህብረ-ባህላዊ ስርዓተ ትምህርቶችን በመቅረፅ ተማሪዎቻችንን ዓለማቀፋዊ ተወዳዳሪ ለማድረግ ዘርፈብዙ ዓለማቀፍ ትስስሮች እንገነባለን፣ እናጠናክራለን
5. **ለተቋማዊ ለውጥ የተጋ አመራርና አስተዳደር ትኩረት መስክ: -** ያገኘናቸውን ድሎች በመጠበቅ የኢንቬስትመንት አቅማችንን ማሳደግና ፋይናንሻል ብቃትን አስተማማኝ ለማድረግ ሁሉንም ባለድርሻዎች እኩል ተጠቃሚ የሚያደርግ ትስስር የመፍጠር ስራ በትኩረት እንሰራለን

**የጅማ ዩኒቨርሲቲመሠረታዊ ዕሴቶች**

- ጥራትና አግባብነት ያለው ትምህርት፣ ምርምርና አገልግሎት (Quality and Relevance)
- የላቀ ብቃት (Excellence)
- ሕብረ-ባህላዊነት፡ መቻቻልና መቀራረብ (Diversity, Tolerance and Inclusiveness)
- ለስርዓተ-ፆታ ትኩረት መስጠት (Gender Sensitivity)
- ተደራሽነትና ፍትሃዊነትን ማስፋት (Equity and Access)
- የመደጋገፍና ቡድን ስሜት (Collegiality and Team Spirit)
- ግልጽነትና ተጠያቂነት (Transparency and Accountability)
- ታማኝነትና ኃቀኝነት (Honesty and Integrity)
- ማህበረሰቡን ማሳተፍና ማስቻል (Community Involvement and Empowerment)
- በትብብርና አጋርነት መስራት (Networking, Collaboration and Partnership)
- ወጪ ቆጣቢነትና ውጤታማነት ዋና ዋናዎቹ የዩኒቨርሲቲው መርህ ናቸው፡፡

## ክፍል ሁለት አጠቃላይ አሃዛዊ መረጃ

### ሠንጠረዥ 1. ስራ ላይ ያሉ ኢትዮጵያዊ መምህራን በትምህርት ደረጃ

| ኮሌጅ | BA, BED, BSc, LLB | | | MA, MSC, MPH, LM | | | MD, DVM, DMD | | | MD+Sp; MPH+Sp; DMD+Sp; DVM+Sp | | | MD+Sub Speciality | | | PHD | | | Total | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር |
| ጤና ኢንስቲትዩት | 75 | 29 | 104 | 216 | 36 | 252 | 113 | 20 | 133 | 59 | 9 | 68 | 5 | 1 | 6 | 21 | 2 | 23 | 489 | 97 | 586 |
| ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ | 37 | 12 | 49 | 98 | 14 | 112 | | | | | | | | | | 36 | 2 | 38 | 171 | 28 | 199 |
| ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት | 188 | 39 | 227 | 119 | 8 | 127 | | | | | | | | | | 8 | | 8 | 315 | 47 | 362 |
| ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ | | | | 12 | 15 | 27 | 69 | 7 | 76 | | | | | | | 10 | | 10 | 91 | 22 | 113 |
| ግብርናና እንስሳት ህክምና | 20 | 14 | 34 | 111 | 21 | 132 | 1 | 3 | 4 | | | | | | | 25 | | 25 | 157 | 38 | 195 |
| ትምህርትና ስነባህርይ | | | | 36 | 4 | 40 | | | | | | | | | | 11 | | 11 | 47 | 4 | 51 |
| ተፈጥሮ ሳይንስ | 28 | 3 | 31 | 124 | 14 | 138 | | | | | | | | | | 12 | 1 | 13 | 164 | 18 | 182 |
| ህግና ገቨርናንስ | 8 | 4 | 12 | 40 | 3 | 43 | | | | | | | | | | 2 | | 2 | 50 | 7 | 57 |
| ጠቅላላ ድምር | 356 | 101 | 457 | 756 | 115 | 871 | 183 | 30 | 213 | 59 | 9 | 68 | 5 | 1 | 6 | 125 | 5 | 130 | 1484 | 261 | **1745** |

### ሠንጠረዥ 2. ስራ ላይ ያሉ ኢትዮጵያዊ መምህራን በአካዳሚክ ደረጃ

| ኮሌጅ | ግራጁዌት ረዳት I እና II | | | ረዳት ሌክቸረር | | | ሌክቸረር | | | ረዳት ፕሮፌሰር | | | ተባባሪ ፕሮፌሰር | | | ፕሮፌሰር | | | ድምር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር |
| ጤና ኢንስቲትዩት | 16 | 9 | 25 | 53 | 15 | 68 | 252 | 47 | 299 | 129 | 17 | 146 | 29 | 3 | 32 | 5 | | 5 | 512 | 106 | 575 |
| ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ | 10 | 4 | 14 | 22 | 6 | 28 | 81 | 14 | 95 | 47 | 2 | 49 | 6 | | 6 | | | 0 | 174 | 30 | 192 |
| ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት | 8 | 8 | 16 | 183 | 39 | 222 | 111 | 8 | 119 | 11 | | 11 | 4 | | 4 | 1 | | 1 | 344 | 57 | 373 |
| ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ | 12 | 14 | 26 | 2 | 1 | 3 | 56 | 5 | 61 | 20 | 2 | 22 | 3 | | 3 | | | 0 | 91 | 22 | 115 |
| ግብርናና እንስሳት ህክምና | 6 | 9 | 15 | 6 | 1 | 7 | 71 | 19 | 90 | 33 | 4 | 37 | 25 | | 25 | 10 | | 10 | 158 | 38 | 184 |
| ትምህርትና ስነባህርይ | | | 0 | 4 | 1 | 5 | 18 | 4 | 22 | 22 | | 22 | 7 | | 7 | | | 0 | 47 | 4 | 56 |
| ተፈጥሮ ሳይንስ | 27 | 2 | 29 | 5 | 2 | 7 | 95 | 13 | 108 | 36 | 2 | 38 | 4 | 1 | 5 | 1 | 0 | 1 | 188 | 17 | 188 |
| ህግና ገቨርናንስ | 3 | | 3 | 5 | 4 | 9 | 41 | 3 | 44 | 6 | | 6 | | | 0 | | | 0 | 51 | 7 | 62 |
| ጠቅላላ ድምር | 82 | 46 | 128 | 280 | 69 | 349 | 725 | 113 | 838 | 304 | 27 | 331 | 78 | 4 | 82 | 17 | 0 | 17 | 1565 | 281 | **1745** |

**ሠንጠረዥ 3. ትምህርት ላይ ያሉ ኢትዮጵያዊ መምህራን**

| ኮሌጅ | እየተማሩበት ያለ ትምህርት ደረጃ | | | | | | | | | | | | Total | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | MA/MSc | | | MD+Spciality | | | Sub-Speciality | | | PHD | | | | | |
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር |
| ጤና ኢንስቲትዩት | 32 | 13 | 45 | 20 | 2 | 22 | 3 | | 3 | 18 | 2 | 20 | 73 | 17 | 90 |
| ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | |
| ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት | 133 | 37 | 170 | - | - | - | - | - | - | 37 | 4 | 41 | 170 | 41 | 211 |
| ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ | 4 | 9 | 13 | - | - | - | - | - | - | 17 | 1 | 18 | 21 | 10 | 31 |
| ግብርናና እንስሳት ህክምና ኮሌጅ | 10 | 10 | 20 | - | - | - | - | - | - | 35 | 6 | 41 | 45 | 16 | 61 |
| ትምህርትና ስነባህርይ | - | - | - | - | - | - | - | - | - | 10 | | 10 | 10 | | 10 |
| ተፈጥሮ ሳይንስ | 4 | 7 | 11 | - | - | - | - | - | - | 41 | 4 | 45 | 45 | 11 | 56 |
| ህግና ገቨርናንስ | 4 | 3 | - | - | - | - | - | - | - | 4 | - | 4 | 8 | 3 | 11 |
| **ድምር** | **187** | **79** | **259** | **20** | **2** | **22** | **3** | | **3** | **162** | **17** | **179** | **372** | **98** | **470** |

**ሠንጠረዥ 4. አዲስ የተቀጠሩ ኢትዮጵያዊ መምህራን**

| ኮሌጅ | BA, BED, BSc, LLB | | | MA, MSC, PH, LM | | | MD, DVM,DMD | | | MD+Sp; MPH+Sp; DMD+Sp; DVM+Sp | | | MD+Sub Speciality | | | PHD | | | Total | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር |
| ጤና ኢንስቲትዩት | - | - | - | 2 | | 2 | - | - | - | - | 1 | 1 | | | | | | | 2 | 1 | 3 |
| ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ | 7 | 3 | 10 | 2 | | 2 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | 9 | 3 | 12 |
| ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት | 15 | 9 | 24 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | 15 | 9 | 24 |
| ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ | 8 | 6 | 14 | 6 | 1 | 7 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | 14 | 7 | 21 |
| ግብርናና እንስሳት ህክምና | 1 | 3 | 4 | 8 | 1 | 9 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | 9 | 4 | 13 |
| ትምህርትና ስነባህርይ | - | - | - | 1 | | 1 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | 1 | | 1 |
| ተፈጥሮ ሳይንስ | 17 | | 17 | 4 | | 4 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | 2 | | 2 | 23 | | 23 |
| ህግና ገቨርናንስ | 3 | 2 | 5 | 1 | 1 | 2 | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | - | 4 | 3 | 7 |
| **ጠቅላላ ድምር** | **51** | **23** | **74** | **24** | **3** | **27** | **0** | **0** | **0** | **0** | **1** | **1** | **0** | **0** | **0** | **2** | **0** | **2** | **77** | **27** | **104** |

**ሠንጠረዥ 5. ስራ ላይ ያሉ የውጭ አገር መምህራን በትምህርትና ፆታ**

| ኮሌጅ | MA,MSc,MPH | | | MD+Sp/ PH+SP/ DMD+SP/ DVM+Sp/ | | | PHD | | | Total | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር |
| ጤና ኢንስቲትዩት | 3 | 2 | 5 | 13 | 3 | 16 | 4 | 2 | 6 | 20 | 7 | 27 |
| ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ | | | | | | | 2 | 1 | 3 | 2 | 1 | 3 |
| ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት | 26 | 1 | 27 | | | | 2 | | | 47 | 2 | 49 |
| ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ | - | - | - | - | - | - | 1 | | 1 | 1 | | 1 |
| ግብርናና እንስሳት ህክምና | - | - | - | - | - | - | 2 | | 2 | 2 | | 2 |
| ትምህርትና ስነባህርይ | - | - | - | - | - | - | | | | | | |
| ተፈጥሮ ሳይንስ | - | - | - | - | - | - | 8 | 0 | 8 | 8 | 0 | 8 |
| ህግና ገቨርናንስ | - | - | - | - | - | - | 1 | | 1 | 2 | - | 2 |
| ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል | 21 | 4 | 25 | 25 | 8 | 33 | | | | 46 | 12 | 58 |
| **ድምር** | 30 | 3 | 33 | 13 | | 16 | 20 | 3 | 21 | 128 | 22 | **150** |

**ሠንጠረዥ 6. የተማሪዎች ቁጥር በባንድ**

| የተማሪዎች ቁጥር በትምህርት ዘርፍ | ወንድ | ሴት | ድምር | የወንድ ሴት ጥንቅር |
|---|---|---|---|---|
| **1. ቅድመ-ምረቃ በመደበኛ** | | | | |
| አዲስ የተመደቡ መደበኛ ቅድመምረቃ ተማሪዎች /በድምሩ | 2887 | 1951 | 4838 | 60:40 |
| **ነባር ተማሪዎች ከ2ኛ ዓመት በላይ** | | | | |
| - ባንድ 1. በኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ ዘርፍ | 4455 | 1814 | 6269 | 71:29 |
| - ባንድ 2. በተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ ዘርፍ | 384 | 367 | 751 | 51:49 |
| - ባንድ 3. በሕክምናና ጤና ሳይንስ ዘርፍ | 2040 | 1001 | 3041 | 67:33 |
| - ባንድ 4. በግብርና ዘርፍ | 776 | 433 | 1209 | 64:36 |
| - ባንድ 5. በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ዘርፍ | 744 | 391 | 1135 | 66:34 |
| - ባንድ 6. በህብረተሰብ ሳይንስና ሂውማኒቲስ ዘርፍ | 887 | 924 | 1811 | 49:51 |
| **ንዑስ ድምር በመደበኛ ቅድመ-ምረቃ** | **12173** | **6881** | **19054** | 63.89 |
| **2. ተከታታይና ርቀት ትምህርት ቅድመ-ምረቃ** | | | | |
| - ማታ | 1975 | 1109 | **3084** | 64:36 |
| - ክረምት | 5103 | 1761 | **6864** | 74:26 |
| - ርቀት ትምህርት | 2141 | 1126 | **3267** | 65:35 |
| **ንዑስ ድምር በተከታታይና ርቀት ትምህርት ቅድመ ምረቃ** | **9219** | **3996** | **13215** | 70:30 |
| **ጠቅላላ ድምር በቅድመ ምረቃ** | **21392** | **10877** | **32269** | 66:34 |
| **3. ሁለተኛ ዲግሪ** | | | | |
| - መደበኛ | **1975** | **315** | **2290** | 86:14 |
| - ማታ | 653 | 241 | **894** | 73:27 |
| - ክረምት | 1495 | 1147 | **2642** | 57:43 |
| - PDDT | 1161 | 1125 | **2286** | 51:49 |
| **ጠቅላላ ድምር በሁለተኛ ዲግሪ** | **5284** | **2828** | **8112** | 65:35 |
| **4. ሶስተኛ ዲግሪ በመደበኛ** | **193** | **13** | **206** | 94:6 |
| **ድምር** | **26869** | **13718** | **40587** | 66:34 |

**ሠንጠረዥ 7. አስተዳደርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች፣ እና ጤና ባለሙያዎች**

| ኮሌጅ | | ከዲፕሎማ በታች | | | ዲፕሎማ | | | BA/BSc/LLB | | | MD/DVM/DMD MA/MSc/MPH | | | Total | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር |
| ጤና ኢንስቲትዩት | | 18 | 84 | 102 | 4 | 34 | 38 | 4 | 18 | 22 | - | - | - | 26 | 136 | 162 |
| ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ | | 1 | 13 | 14 | 5 | 37 | 42 | 4 | 15 | 19 | - | - | - | 10 | 65 | 75 |
| ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት | | 204 | 770 | 974 | 7 | 17 | 24 | 22 | 31 | 53 | 2 | 1 | 3 | 236 | 818 | 1054 |
| ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ | | | 56 | 56 | 6 | 24 | 30 | 5 | 12 | 17 | - | - | - | 11 | 92 | 103 |
| ግብርናና እንስሳት ህክምና ኮሌጅ | | 214 | 229 | 443 | 25 | 55 | 80 | 14 | 20 | 34 | - | - | - | 254 | 304 | 558 |
| ትምህርትና ስነባህርይ | | 1 | 9 | 10 | 1 | 17 | 18 | 5 | 11 | 16 | - | - | - | 7 | 37 | 44 |
| ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል | ጤና ባለሙያ | - | - | - | 162 | 130 | 292 | 206 | 181 | 387 | 43 | 11 | 54 | 411 | 322 | 733 |
| | አስተዳደር | 293 | 246 | 539 | 76 | 74 | 149 | 26 | 23 | 49 | 3 | 1 | 4 | 398 | 344 | 742 |
| ተፈጥሮ ሳይንስ | | 3 | 72 | 75 | 5 | 26 | 31 | 3 | 7 | 10 | 0 | 0 | 0 | 11 | 105 | 116 |
| ህግና ገቨርናንስ | | 2 | 7 | 9 | | 14 | 14 | 10 | 11 | 21 | - | - | - | 3 | 31 | 34 |
| ዋናው ግቢ | | 452 | 1236 | 1688 | 166 | 24 | 166 | 171 | 112 | 283 | 15 | 3 | 18 | 804 | 1591 | 2395 |
| **ጠቅላላ ድምር** | | **1188** | **2722** | **3910** | **457** | **428** | **884** | **470** | **441** | **911** | **63** | **16** | **79** | **2171** | **3845** | **6016** |

**ሠንጠረዥ 8. አዲስ የተቀጠሩ፣ በዝውውር የመጡ፣ የተሰናበቱ የመንግሥት ሠራተኞች**

| ቋሚ የመንግሥት ሠራተኞች | | ብዛት |
|---|---|---|
| አዲስ የተቀጠሩ | ማህበረተሰብ ተኮር ሬዲዮ ጣቢያ ሪፖርተር | 4 |
| | ሾፌር II | 12 |
| | ወጥ ቤት ሠራተኛ | 65 |
| | ክሊኒካል ደራጊስት | 2 |
| | ክሊኒካል ነርስ | 4 |
| | ላቦራቶሪ ቴክኒሻን | 2 |
| | ጀማሪ ፋርማሲስት | 1 |
| | ፖርተር | 48 |
| | ጽዳት | 2 |
| በዝውውር፣ በሹመትና በትዕዛዝ ወደ መ/ቤቱ የመጡ ሠራተኞች | | 4 |
| በልዩ ልዩ ምክንያት ከመሥሪያ ቤቱ የተሰናበቱ ቋሚ ሠራተኞች | | 56 |
| የደረጃ ዕድገት ያገኙ ሠራተኞች | | 81 |
| **ድምር** | | **280** |

**ሠንጠረዥ 9. ፋሲሊቲ ዝርዝር**

| ኮሌጅ | የመማሪያ ክፍል ብዛት | | መደበኛ ላቦራቶር | ኢንተርኔት ካፌ | ኩር ላቦራቶር | ቤተመፃህፍት | የተማሪ ካፊቴሪያ | የተማሪ መኝታ ክፍሎች | የተማሪዎች ክሊኒክ | ወርክሾፖች ብዛት | የመሬት ስፋት በሄክታር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | Smart class | Non-smart calss | | | | | | | | | |
| ዋናው ካምፓስ | | | | | | | | 1475 | 1 | | 76 |
| 1. ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት | 42 | 70 | | | | 2 | | 1100 | 1 | | 294 |
| 2. ጤና ኢንስቲትዩት | 28 | 19 | 15 | 2 | | 5 | | | | 1 | |
| 3. ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ | 16 | 10 | | | | | | | | | |
| 4. ትምህርትና ስነባህርይ | 8 | 4 | 2 | | | 0 | | | | | |
| 5. ተፈጥሮ ሳይንስ | 18 | 6 | 20 | | 0 | 1 | 0 | | 0 | | |
| 6. ህግና ገቨርናንስ | 10 | 3 | | | | 1 | | | | | |
| 7. ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ | 19 | 0 | 3 | | 0 | 2 | 0 | 349 | 0 | | 2.4 |
| 8. ግብርናና እንስሳት ህክምና | 26 | 0 | 3 | 0 | | 2 | 4 | 197 | 1 | 2 | 109 |
| **ድምር** | **167** | **112** | **43** | **2** | **0** | **13** | **4** | **2772** | **3** | **3** | **503** |

## ፕሮግራም አንድ- የስራ አመራርና መልካም አስተዳደር

ቀልጣፋና ውጤታማ አስተዳደራዊ ስርዓት ዕውን በማድረግና ፈጣንና ወቅታዊ ምላሽ በመስጠት የአካዳሚክ፣ ምርምሩን፣ ማህበረሰብ አገልግሎትና የዓለማቀፋዊነት ግቦችን ማሳካት ይቻላል፡፡ በተጨማሪም የንድግ ማዕከላትን በመክፈት፣ የማማከር ስራዎችን በመስራት፣ የአዕምሮ ኃብቶችን በማፍለቅና በመሸጥ እንዲሁም ከልማት አጋሮች ጋር በጋራ በመስራት ዩኒቨርሲቲው የራሱን አማራጭ የገቢ ምንጮች ለማጎልበት ተግቶ ይሰራል፡፡ እነዚህን ግቦች ለማሳካት የሚከተሉት ስራዎች ተከናውነዋል፡፡

### ዓላማ 1.1. የሰው ኃብት ልማትና ተቋማዊ አመራርን ማሻሻል

**ሠንጠረዥ 10. የሰው ኃብት ልማት ልማትና ተቋማዊ አመራርን ማሻሻል**

| ቁልፍ የአፈፃፀም ማሳያዎች | መለኪያ | የዓመቱ ዕቅድ | የ1ኛ ሩብ ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | በመቶኛ |
| አጭርና ረጅም ጊዜ ስልጠና ያገኙ መምህራን | ቁጥር | 1750 | 700 | 505 | 72 |
| የሰው ኃብት ልማት ክህሎት ዳሰሳ skill inventory | ቁጥር | 2 | 1 | 0 | 0 |
| የአስተዳደር መረጃ ስርዓት/ MIS መሰረት ያደረጉ ፕሮግራሞች | መቶኛ | 100 | 75 | 60 | 80 |
| በደረጃ ዕድገት የተመደቡ አስተዳደር ሠራተኞች ብዛት | ቁጥር | 325 | 81 | 81 | 100 |
| የተቀጠሩ አስተዳደር ሠራተኞች ብዛት | ቁጥር | 140 | 140 | 140 | 100 |
| በዝውውር የመጡ የአስተዳደርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች | ቁጥር | 12 | 4 | 4 | 100 |
| የስራ ስምሪትና ቁጥጥር smart ቴክኖሎጂ | መቶኛ | 100 | 50 | 30 | 60 |
| የቅጥር ማስታወቂያና የአመልካቾች ምዝገባ smart ቴክኖሎጂ | መቶኛ | 100 | 30 | 30 | 100 |
| የሰራተኞች ስራ አፈፃፀም ምዘና፣ ፍቃድ አጠያየቅና መፍቀጃ | መቶኛ | 100 | 25 | 25 | 100 |
| የተዘጋጀና የተተገበረ ደንበኞች አገልግሎት ስታንደርድ | ቁጥር | 1 | 1 | 1 | 100 |
| የኮምፒውተር ላቦራቶሪዎችን ማቋቋም | ቁጥር | 3 | 2 | 1 | 50 |
| የአይሲቲ ባለሙያዎች የቴክኒክ ስልጠና | ቁጥር | 17 | 7 | 41 | 586 |
| የመማሪያ ክፍሎችን ጠግኖ ለመማር ማስተማር ዝግጁ ማድረግ | መቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 |
| የተማሪዎች መመገቢያ አደራሾችን ጠግኖና አዲሶ ዝግጁ ማድረግ | መቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 |
| የተማሪዎች መኖሪያ ጠግኖና አዲሶ ማዘጋጀት | መቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 |
| የተማሪዎች አገልግሎት መስጫ ማዕከላቶችን ዝግጁ ማድረግ | መቶኛ | 100 | 25 | 25 | 100 |
| የግቢ ውበት መጠበቅ | መቶኛ | 100 | 25 | 25 | 100 |
| የምግብ አቅርቦት ጨረታ ወጥቶ ለተማሪዎች ማቅረብ | መቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 |
| አመታዊ ግዥ ፍላጎት ማቅረብ | መቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 |
| አመታዊ ጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ማዘጋጀት | መቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 |
| አመታዊ ፕሮግራም በጀት መርሃ ግብረ አዘጋጅቶ ማቅረብ | መቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 |
| ለኮሌጆች በጀት ድልድል ማከናወን | መቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 |
| ለመማር ማስተማር ግብአት ግዥ ግልፅ ጨረታ ማውጣት | መቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 |
| የሰው ኃይል ቅጥርና ድልደል | ቁጥር | 225 | 108 | 108 | 100 |
| የ2009 ዓ.ም ፋይናንሻል ኦዲት ማከናወን | መቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 |
| የ2009 ዓ.ም የንብረት ቆጠራ ኦዲት ማከናወን | መቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 |
| መሰረተልማቶችን ማሟላት (ውሃ፡ ኤሌክትሪክ ስልክ) | መቶኛ | 100 | 25 | 25 | 100 |
| Attrition Rate | | | | | |
| - ሀኪም | መቶኛ | 0.05 | 0.0125 | 0.001 | 8 |
| - ነርሶች | መቶኛ | 0.05 | 0.0125 | 0.0008 | 6.4 |
| - ፋርማሲስት | መቶኛ | 0.05 | 0.0125 | 0.00072 | 5.76 |
| - የሰመመን ባለሙያ | መቶኛ | 0.05 | 0.0125 | 0.0006 | 4.8 |
| - የአስተዳደር ሰራተኛ (All Type) | መቶኛ | 0.05 | 0.0125 | 0.0012 | 9.6 |
| - ላቦራቶሪ ቴክኒሺያኖች | መቶኛ | 0.05 | 0.0125 | 0.0004 | 3.2 |

**በሰው ኃብት ልማት ልማትና ተቋማዊ አመራር የተሰሩ ዝርዝር ተግባራት**

- መማሪያ ክፍሎች ታድሰው ለአገልግሎት ዝግጁ ሆነዋል፤ የተማሪዎች መመገቢያ አዳራሽ፣ የውሃ፣ መብራትና ሌሎች መሰረተ-ልማት አገልግሎቶች እንዲያገኙ ተደርጓል
- በክረምት ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ተማሪዎች ሳይጉላሉ ሁሉንም አገልግሎቶች በወቅቱና በጥራት እንዲያገኙ ተደርጓል
- የተማሪዎች ክሊኒክ አገልግሎት የተሻለ አገልግሎት እንዲሰጥ የውስጥ ግብዓት ተሟልቷል፤ ተማሪዎች ወደ መደበኛ ትምህርታቸው ከመመለሳቸው በፊት ዝግጁ ሆኗል
- በዚህ ዓመት የከፈትናቸው 28 ድህረ ምረቃ ትምህርት ፕሮግራሞች ላይ የሚሰሩ የምርምር ውጤቶች ታላቅ ገፀበረከት ያቀርባሉ
- ባሉን ምቹ መሠረተ ልማቶችና ተስማሚ ምሁራዊ አካባቢ እንዲሁም ከውጭ አገር የፋይናንስ አቅራቢዎች ያለን በጎ ገፅታ የተሻለ ገፅታ በምርምር እንድንልቅ ረድተውናል
- የግቢው ውበት እንዲሻሻልና እንዲጠበቅ በማድረግ የተሻለ የመማር ማስተማር አካባቢ ተፈጥሯል
- ለአካል ጉዳተኞች አመቺ የመማር ማስተማር አካባቢ ለመፍጠር መንገዶች፤ ቤተሙከራዎችና ሌሎች አገልግሎት መስጫዎች እንዲመቻቹ ተደርጓል
- ላቦራቶሪ፣ ፖሊስ ቢሮ፣ ተማሪዎች ክሊኒክ፣ ጋራጅ፣ መምህራን መኖሪያ ቤትና ቢሮ፣ የተማሪዎች ምግብ ቤት የጣራ ፍሳሽ ስራ ተሰርቷል፤
- የድህረምረቃ ተማሪዎች መዝናኛ ክበብ፣ ሽንት ቤት፣ ምግብ ቤት፣ እርሻና ፅዳት ማሽኖች፣ መዝናኛ ክበብና መማሪያ ክፍሎችና ወንበር ዕድሳትና ጥገና ተደርጓል
- OTRS ላይ የተመዘገቡ ስራዎች በአግባቡ ተሰርተዋል
- በትምህርትና ስነባህርይ ኮሌጅ ከ12,500 በላይ የትምህርት መርጃ ሞጁሎች ተባዝተውና ተዘርዘው ተከፋፍለዋል
- ባሉት ክፍት ስራ የመደቦች የደረጃ ዕድገት ማስታወቂያ በማውጣት ሰራተኞች በውድድር ተመድበዋል
- የዕቃ ግምጃ ቤትና የትምህርት ክፍሎችን በካይዘን ፍልስፍና መሰረት የማደራጀት ስራ ተሰርቷል
- የ1ለ5 ቡድኖች በአዲስ መልክ በማደራጀት ደንበኛ ተኮር አገልግሎት ተሰጥቷል፣ የትምህርት ልማት ሠራዊት (Team work) ተደራጅቷል

**የጅማ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ህብረት**

- በዋና ግቢ 18፣ እንዲሁም በኪቶ ፉርዲሳና ግብርናና እንስሳት ህክምና ካምፓሶች በእያንዳንዳቸው ከ15 በላይ ክበባት ያሉት የጅማ ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች ህብረት ሶስት መማክርቶች አሉት። እነዚህም የቴክኖሎጂ ኢንስቲቲዩት ተማሪዎች መማክርት፣ የግብርናና እንስሳት ህክምና ኮሌጅ ተማሪዎች መማክርትና የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ተማሪዎች መማክርት ናቸው። የህብረቱ ዓላማ ተማሪዎችን በማዝናናት ለሰላማዊ መማር ማስተማር ስኬት ጉልህ ሚና መጫወት ነው።

- ከላይ የተጠቀሱት ክባበት የየራሳቸውን ንዑስ ዓላማዎች በመቅረፅ እየሰሩ ሲሆን ዝርዝራቸው እንደሚከተለው ተቀምጧል። እነዚህም ቻሪቲ፣ ፀረ-ኤች አይ ቪ ኤድስ፣ ስነ ምግባርና ፀረ-ሙስና፣ ተማሪ ኔት ዶት ኮም፣ ስፖርትና መዝናኛ፣ GDASAO፣ ላይብራሪ፣ ስነጾታ፣ ሰብኣዊ መብት፣ አካባቢ ጤና ጥበቃ፣ ግራንድ ምግብ ኮሚቴ፣ በጎፈቃደኛ ደህንነት፣አምባሳደር፣ አርት፣ ሰላምና ፍቅር፣ አቻ ለአቻ፣ ዘላቂ ውይይትና ምክር አገልግሎት ክበባት ናቸው።

- ክበባቱ ስራ ከመጀመራቸው በፊት የአመቱን ዕቅድ በማውጣት ዩኒቨርሲቲው የመደበላቸውን በጀት የሚጠቀሙ ሲሆን የሚያስተሳስራቸውም ለዩኒቨርሲቲዉ ሰላማዊ መማር ማስተማር ስኬታማነት በጋራ መስራት ነው።

- የተማሪዎች ህብረት ጠቅላላ አገልግሎት ከተማሪዎች መሰረታዊ ፍላጎት አብዛኛውን ድርሻ የሚይዝ ዘርፍ ሲሆን ይህም በዋናነት የምግብ፣ ውሃ፣ መኝታና ህክምና አገልግሎቶች በጥሩ ሁኔታ እየተሰጠ መሆኑን ሪፖርት አቅርቧል። በእያንዳንዱ ብሎክ ኤርያል

ማስተርና ብሎክ ማስተር በማደራጀት ሰላማዊ መማር ማስተማርና የአገልግሎት ጥራት ላይ ከፍተኛ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ቀደም ሲል የነበረው የዲኤስቲቪ ችግር አሁን ሙሉ- በሙሉ ተቀርፏል

## ዓላማ 1.2. መልካም አስተዳደርን ማሻሻልና ማስፈን

**ሠንጠረዥ 11. መልካም አስተዳደርን ማሻሻልና ማስፈን**

| ቁልፍ የአፈፃፀም ማሳያዎች | መለኪያ | የዓመቱ ዕቅድ | የ1ኛ ሩብ ዓመት | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | በመቶኛ |
| ለአብያተ መፅሃፍት ሰራተኞች የተሰጠ የተሀድሶ ስልጠና | ቁጥር | 343 | 343 | 304 | 89 |
| የአብያተመጽሀፍት ተጠቃሚ (አንድ ተጠቃሚ በተመላለሰ ቁጥር ይቆጠራል) | ቁጥር | 1,000,000 | 250,050 | 250,000 | 99.98 |
| በማህበረሰብ ሬዲዮ (በንባብ እንኑር ፕሮግራም የተላለፉ ፕሮግራሞች) | ቁጥር | 48 | 12 | 12 | 100 |
| የኢንፎርሜሽን ሊትረሲ ስልጠና (ለድህረ ምረቃ ተማሪዎች) | ቁጥር | 600 | 200 | 115 | 58 |
| ነዳጅ ለተሽከርካሪ፣ ትራክተር ጀኔሬተርና ስብሰባ ለመጡ እንግዶች | ሊትር | 529,991 | 132,497 | 83,011 | 63 |
| - የመሪ ዘይት | ሊትር | 200 | 50 | 50 | 100 |
| - የባትሪ ውሃ | ሊትር | 200 | 50 | 38 | 76 |
| - የፍሬን ዘይት | ሊትር | 150 | 37.5 | 30 | 80 |
| - የካምቢዮ ዘይት | ሊትር | 200 | 50 | 53 | 106 |
| - ግሪስ | በኪሎ | 1500 | 375 | 83 | 22 |
| - ቱቲ | ሊትር | 400 | 100 | 30 | 30 |
| ለኢንሹራንስና የእርጅና ዋጋ | ቁጥር | 173 | 45 | 0 | 0 |
| ተሽከርካሪ እጥበትና ቅባት በውጭ ለባጃ አገልግሎት | ቁጥር | 156 | 468 | 300 | 64 |
| የተሽከርካሪ ብቃት ምርመራ፣ ክላውዶና መንገድ ፈንድ ክፍያ | ቁጥር | 173 | 45 | 0 | 0 |
| ለመካኒኮች፣ ሹፌርና ረዳቶች ስልጠና | ቁጥር | 48 | 12 | 0 | 0 |
| መምህራን፣ ሠራተኞችና ተማሪዎች ለሥራ ሲወጡ ማስተናገድ | ቁጥር | 3000 | 750 | 0 | 0 |
| T.T.P፣ CBTP፣ DDTP ተማሪዎች ሲወጡ ማስተናገድ | ቁጥር | 9692 | 2423 | 2000 | 83 |
| ሙሉ የሞተር እድሳት | ቁጥር | 3 | 1 | 0 | 0 |
| አጠቃላይ የቦዲና ወንበር እድሳት | ቁጥር | 8 | 2 | 1 | 50 |
| መለስተኛ ጥገና ሠርቪስ ማድረግ | ቁጥር | 1788 | 447 | 447 | 100 |
| ካምፓኒ ለሚጠገኑና ከ5 ዓመት በታች ለሆኑ ተሽከርካሪዎች ጥገና | ጥቅል | 36 | 9 | 2 | 22 |
| **የቅሬታና የዲሲፒሊን ሂደቶች** | | | | | |
| - ቅሬታ ያቀረቡናቅሬታየተፈታላቸዉሠራተኞች ብዛት | ቁጥር | 50 | 16 | 4 | 25 |
| - ምላሽ ያገኙ/ የተስተናገደ ቅሬታና አቤቱታ | ቁጥር | 50 | 16 | 4 | 25 |
| - ተገልጋዩ ህብረተሰብ ቅሬታውን የሚያቀርብበት የቢሮ አመላካች መለጠፍ | ቁጥር | 8 | 4 | 4 | 100 |

### ከጅማ ከተማ መስተዳድር ጋር የተሰሩ ስራዎች

- ሆስፒታሊቲና ቱሪዝም ኢንስቲትዩት ግንባታ የሚከናወንበት ቦታ ርክክብና ካሳ ግምት ስራ ግምት ተሰርቷል፣ ከግንባታ ቦታ ለሚነሳው የኦሮሚያ መንገዶች ባለስልጣን ምትክ ቦታ ርክክብ ተደርጓል
- የፍሳሽ ማብላያ ገንዳ በሚከናወንበት 200 ሜትር ራዲየስ ውስጥ የሚገኙ ተነሺዎች የቤት፣ አትክልት ግምት ሥራ ተሰርቶ ተጠናቋል፤ ለተነሺዎች ምትክ ቦታ ለመስጠት ተለይቷል፣ በፐሎት የማከፋፈል ሂደት በቀጣይ ይከናወናል፡፡
- የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ ማስፋፊያ ቦታ ርክክብና ካሳ ክፍያ ግምት ተሰርቷል፣ ቦታ ርክክብ በቀጣይ ይከናወናል፡፡
- በጊንጆ ትምህርት ቤት በኩል የሚገኘውን የዋና ግቢ አጥር መስሪያ ቦታ ወሰን መለየት ሥራ እየተሰራ ነው፤ ለቤት ካሳ ግምት መረጃ ተወስዷል

- የሪሃብልቴሽን ሴንተር ግንባታ ማከናወኛ ቦታ ርክክብና የካሳ ክፍያ ዝግጅት ሥራ 25% ተጠናቋል፣ በኪቶ-ፉርዲሳ ንብ እርባታ በኩል የሚገኘው አጥር መስሪያና ይዞታ የማስወሰን ሥራ በቀጣይ ይከናወናል፡
- የሳር-ሰፈርና ቆጪ ሳይቶች ኮንዶሚኒየም ቤቶች ይዞታ 100 በመቶ ሳይት ፕላን ተረክበናል፣ ስፖርት ካፌ አጠገብ የሚሰራዉ ገስት ሃውስ ሳይት ፕላንና የግንባታ ፍቃድ የማግኘት ስራ በቀጣይ ይከናወናል

**ጨረታ እንዲወጣ ለግዥና ንብረት አስተዳደር ጥያቄ የቀረቡ**

ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ስራዎች ጨረታ እንዲወጣባቸው ቀርበዋል፤

- በሰኮሩ ወረዳ የሳሊኒ ካምፕ ውሃ መጠራቀሚያ ድጋሚ ጨረታ፣ የፍሳሽ ማብላያ ገንዳ የስራ ዝርዝር ዲዛይንና ዶክመንት ዝግጅት፣
- የኪቶ-ፉርዲሳ ሁለተኛ ዙር የተማሪዎች ማደርያ ሕንፃ ዲዛይንና ዶክመንት ዝግጅት፣
- የዋና ግቢ ቤተ-መፃሃፍት ዲዛይንና ዶክመንት ዝግጅት፣
- የግብርናና እንስሳት ህክምና ኮሌጅ ድህረ-ምረቃ ሕንፃ ሥራ፣
- በአጋሮ ካምፓስ የተቋረጠ ፕሮጀክት ሥራ ማስቀጠል፣
- የሰኮሩ የመስክ ምርምር ማዕከል፣
- የደረቅ ቆሻሻና የምግብ ትርፍራፊ ማስወገጃና ማብላያ፣
- የኪቶ ፉርዲሳ ገቢ ማመንጫና ኮሚኒቲ ትምህርት ቤት ግንባታ፣
- በዋናው ጊቢ የጋራጅ (Car maintenance and repair center) ፣
- በዋናው ጊቢ የ Central Store construction፣
- ዶክተርስ ዲዩቲ ብሎክስ (የጤና ቱሪዝም ልማት ፕሮጀክት) ፣
- በኪቶ ፉርዲሳ የቀለበት መንገድ ሥራ ለሦስተኛ ጊዜ፣
- በዋና ጊቢ ከኮሚኒቲ ትምህርት ቤት እስከ ስፖርት ማዘውተሪያ ያለ የጀርባ አጥርና
- የኪቶ-ፉርዲሳ ሁለተኛ ቤተ-መፃህፍት ሕንፃ ዲዛይንና አማካሪ ድርጅት ጨረታ እንዲወጣ ለግዥና ንብረት አስተዳደር ጥያቄ ቀርቧል

**የዲዛይንና ዶክመንት ዝግጅት እየተደረገ ያለ**

- በሰበታ ከተማ የሚሰራ የዩኒቨርሲቲ ላይዘን ቢሮ፣ የአዕምሮ ሕሙማን ሕክምና መስጫና ማገገሚያ ማዕከል፣ በዋናው ግቢ የሚሰራ ኤሌክትሪክ ኃይል ማሰባሰቢያ፣ የዩኒቨርስቲ መግቢያ በሮች (ቢዝነስ ኮሌጅ፣ ግብርና ኮሌጅና ኪቶ-ፉርዲሳ ካምፓስ) ለመስራት የዲዛይንና ዶክመንት ዝግጅት እየተደረገ ነው፤ የዋናው ግቢ በር ደግሞ እየተሰራ ነው

**እየተገመገመ ያለ የፋይናንሻል የጨረታ ዶክመንት**

- ዋና-ጊቢ፣ ኪቶ-ፉርዲሳ፣ አጋሮ ካምፓስና የቀድሞ ሳሊኒ ካምፕ የጉርጓድ ውሃ ቁፋሮ ስራ፣ ኮሚኒቲ ትምህርት ቤት የተማሪዎች መማሪያ ክፍል፣ በኪቶ ፉርዲሳ ካምፓስ የስፖርት ማዘውተሪያ የቴክኒካል ጨረታ ሰነዶቻቸው እየተገመገሙ ነው።

**ወደስራ የተገባ ግንባታ**

- የሆስፒታል ቆሻሻ ማቃጠያ (Incinerator) ፣ ሰኮሩ ወረዳ የቀደሞ ሳሊኒ ካምፕ መንገድ፣ አጥር፣ የመሰብሰብያ አዳራሽና ጥገና ሥራ፣
- የኪቶ ፉርዲሳ የተማሪ መዝናኛ ክበብ በቡኤልኮን ጣምራ ሲአርሲ ኮንስትራክሽን በለውጥ ሥራ ትዕዛዝ እንዲሰራ ውሳኔ ተላልፏል

**ቅሬታና አቤቱታን መቀነስ**

- ከሃሳብ መስጫ ሳጥን፣ ስልክና በአካል የሚደርስ ጥቆማ ተቀብሎ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን የማጣራት ስራ እየተሠራ ይገኛል፡
- ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል ስትራቴጂ ተዘጋጅቷል፣ ፖስተሮች ተለጥፈዋል፣
- የአራተኛ ሩብ ዓመት ህጋዊነት (ፋይናንስ ኦዲት) ምርመራ ሪፖርት ለሚመለከተው አካል ቀርቧል። ግብረ-መልስ ተሰጥቷል፡
- የላይዘን ቢሮ የግዥ ሰራተኛ ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት ለሚመለከተው አካል ማስተካከያ እርምጃ ቀርቧል። የጎደለው ገንዘብ ተተክቷል።

- በገቢ ማመንጨ ማዕከላት የቁጥጥር ስርዓትን ለማጠናከርና ብክነትን ለመቀነስ ህጋዊ ሰነዶችን ለማሳተም ጥረት እየተደረገ ነው፣ በአንድ የግብር መለያ (መክፈያ) እንዲሰሩ ለማድረግ ከህግ ዳይሬክቶሬት ጋር በመሆን ሥራ እየተሰራ ነው።
- በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ የደንበኞች አገልግሎት ስታንደርድ ተለጥፎ ስራ ላይ ውሏል፣ ከደንበኛ በሚገኝ ግብረ-መልስ እያስተካከልን እንገኛለን
- የተመደበልንን በጀት በአግባቡ በመጠቀም ለመማር ማስተማሩ የሚያስፈልጉ ግብአቶችን በጥራት ለማቅረብ እየሰራን ነው
- የላቀ ውጤት ላመጡ መምህራንና ሰራተኞች የሽልማት ኘሮግራም ተካሂዷል
- በየስራ ክፍላቸው በአፈጻጸማቸው ጥሩ ውጤት ላስመዘገቡ አስተዳደር ሰራተኞች የማበረታቻ ሽልማት ተሰጥቷል፡

**የተቋማዊ ለውጥ ማሻሻያዎችን ማዘጋጀትና ስራ ላይ ማዋል (አደረጃጀት፣ የለውጥ መሳሪያዎች)**

- ከኮሌጆችና ስራ ክፍሎች የዓመቱን ግዢ ፍላጎት በማሰባሰብ የተዘጋጀ የግዥ ዕቅድ ለመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በወቅቱ ተልኳል
- የትያትር ትምህርት ክፍል ዕቃዎች፣ የሁለት ኢንስቲትዩቶች የህክምና ዕቃና የህትመት አገልግሎት ግዢ ሰነድ ግምገማ ተጠናቋል፡
- ከአሸናፊ አቅራቢ ድርጅቶች የቀረቡ የሙዚቃ ትምህርት ክፍል ዕቃዎች፣ የጤና ኢንስቲትዩት የላቦራቶሪ ዕቃዎች፣ የመታወቂያ ማዘጋጃ ቁሳቁስ ግዢ ተፈፅሞ ርክክብ ተጠናቋል፡
- ከሄልዝ ኬር ፋይናንሲንግ በተሰጠ አገልግሎት በድምሩ ብር 834,128 ገቢ ተደርጓል
- በግብርና ኮሌጅ ለኃላፊዎች ወንበርና የውጭ ቢሮ መጠቆሚያ ተሰርቷል፣ የኮሌጁን ገፅታ የሚያሳዩ ባነሮች ለተለያዩ ፕሮግራሞች ታትመዋል፣ ከ20 በላይ አዝናኝና አስተማሪ የፕላዝማ ቪዲዮች ተሰርተዋል፣ በftp, Samba server, DHCP, DNS, Proxy configuration ስልጠና ተሰጥቷል፣ አዲስ የውሃ መስመር ተገጥሟል፣ የተበላሹ መስመሮች ተጠግነዋል፣ የውሃ ሞተር ዕድሳት ተደርጓል፣ 230 ኮምፒውተሮች ጥገና ተደርጓል፣
- BSCን ለመተግበር ከመምህራን ጋር ውይይት በማድረግ ሰፊ ስራ ተሰርቷል፣
- Whiteboard ጥገና ተከናውኗል፤ የመማሪያ ክፍሎች ቀለም ተቀብቷል
- በተማሪዎች ኮምፒውተር ላቦራቶሪ ፣በተማሪዎች ካፌ ተበጥሶ የነበረ Fiber ጥገና በማድረግ ስራ ተጀምሯል
- ኢ-ለርኒንግ ለማጠናከር ተጨማሪ ኮምፒውተርና ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን ካሜራ በመግጠም ለመማር ማስተማር ዝግጁ ተደርጓል

**በህግ አገልግሎት**

- ጅማ ዩኒቨርሲቲ ከሳሽ ከሆነባቸው ዘጠኝ መዝገቦች ሁለቱ ለዩኒቨርሲቲው ተፈርዶ መዝገባቸው የተዘጋ ሲሆን በሰባቱ ቀጠሮ ተይዞ ክርክር ላይ ነው። በተመሳሳይ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ከተከሰሰባቸው አራት ክሶች አንዱ ለዩኒቨርሲቲው ተፈርዶ የተወሰነ ሲሆን በዚህም ቦንድ ለመውረስ ቀጠሮ ላይ ነን።

**ላይዘን ቢሮ**

- 45 የውጭ መምህራንና ተማሪዎች ጊዜያዊ የመኖሪያ ፈቃድ እንዲያገኙ፣ 25 የውጭ ዜጎች ቪዛና የመድረሻ ቪዛ እንዲያገኙ ተደርጓል
- ከዙህ በታች የተዘረዘሩ በእርዳታ የተገኙና ዕቃዎች ወደአገር ውስጥ እንዲገቡ ተደርጓል፣ ዕቃዎቹም: - ለጁካን ፕሮጀክት የላቦራቶሪ ዕቃዎች፣ ለስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የህክምና ዕቃ፣ ለሶሻል ሳይንስ ኮሌጅ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች፣ ለቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የህክምና ዕቃ፣ ለሕክምና ሳይንስ ፋካልቲ ህክምና ዕቃና ለጤና ሳይንስ ምርምር የህክምና ዕቃ በዕርዳታ የተገኙ ሲሆን ለዚህም አስፈላጊው ቀረጥ ተከፍሎ ወደአገር ውስጥ ገብተዋል፡

- ከሉሲ ኮንሰልቲንግ ኢንጂነርስ ጋር በመተባበር የመጀመሪያው አገር አቀፍ የመንገድ ደህንነት ኮንፍረንስ በአዲስ አበባ ተከናውኗል፣ ስለኮንፍረንሱ ጋዜጣዊ መግለጫ ተሰጥቷል፤ የገፅታ ግንባታ ሥራ ተከናውኗል፡፡ በርካታ ጋዜጦች፣ የኤፍኤምና ብሔራዊ ራዲዮ ቴሌቪዥን ጣቢያዎች ዜናውን በስፋት ዘግበዋል
- ከአይ ካፒታል ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር የመጀመሪያው የሰው ሀብት ልማት ኮንፍረንስ የተሳካ እንዲሆን ድጋፍ ተደርጓል፡፡
- ከ ABH ጋር በመተባበር የተማሪዎች ምረቃ የተሳካ እንዲሆንና የገፅታ ግንባታም እንዲሠራ ተደርጓል
- አብረውን ለሠሩ ሚድያ ድርጅቶች ምስጋና ደብዳቤ ተሰጥቷል (ኢቢሲ፣ ኢሬቴድ፣ ኢዜአ፣ አዲስ ቲቪ አዲስ አድማስ፣ ሪፖርተር፣ ቁምነገር መፅሔት)
- ዩኒቨርሲቲውን የሚያስተዋውቁ ዜናዎችና ማስታወቂያዎች በኢቢሲና ፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት እንዲተላለፉ ተደርጓል፡፡
- ሜድካል ሴንተር አዲስ ያስገነባው የኤሌትሪክ ኢንሲኔሬተር የተገጠመ ሲሆን የባለሙያዎች ስልጠና ለመጀመር በሂደት ላይ ይገኛል ፡፡
- የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና FMAC በሰጡት የማስተካከያ ጥያቄዎች ለህመምተኞች የዕቃ ማጠቢያ ሲንኮች ተሰርቷል፣

## ዓላማ 1.3. የገቢ ማመንጫ ዘርፎችንና የፋይናንስ አስተደዳርን ማጎልበት

### ሠንጠረዥ 12 .የተለያዩ የገቢ ምንጮችን ማፈላለግና ማሳደግ

| ቁልፍ የአፈፃፀም ማሳያዎች | መለኪያ | የዓመቱ ዕቅድ | የ1ኛ ሩብ ዓመት | | የሩብ ዓመት አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | |
| **የአይሲቲ ኢንተርፕራይዝ ለማቋቋም** | | | | | |
| - ህጋዊ አካሄድ ማስጨረስ | መቶኛ | 100 | 20 | 25 | 125 |
| - የስራ ቡድን ማቋቋም | መቶኛ | 100 | 25 | 25 | 100 |
| - ሲስኮ አካዳሚን እንደገና ማጠናከር | መቶኛ | 50 | 15 | 15 | 100 |
| - ሶፍትዌር ልማት ጨረታ ውድድር መሳተፍ | ጨረታ ቁጥር | 1 | 0 | 0 | 0 |
| - የኔትወርክ መሰረተልማት ዝርጋታ ጨረታ ላይ መሳተፍ | ጨረታ ቁጥር | 1 | 0 | 0 | 0 |
| **ኢላዳሌ እርሻ ጣቢያ** | | | | | |
| - የማገዶና ኮንስራክሽን እንጨት፣ ጀንፈል ቡና | የተገኘ ገቢ በብር | 2,000,000 | 750,000 | 722,680 | 96 |
| - አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ የተለያዩ ችግኞች | የተገኘ ገቢ በብር | 150,000 | 50000 | 45,902 | 92 |

### የገቢ ምንጮችን ለማጎልበት የተከናወኑ ስራዎች

- የቀድሞውን ማተሚያ ቤት ማሽን ተከላና አስጠግኖ ሥራ ለማስጀመር የማሽኖቹ ሁኔታ በባለሙያ ተለይቷል፤ ስራውን በቴክኒክ የሚመራ ባለሙያ ቅጥር በኮንትራት ለመፈጸም በሂደት ላይ ይገኛል፡፡ በቅርቡ ወደስራ ይገባል፡፡
- ከመከላከያና ኢንጅነሪንግ የተገዙ ሰባት ሻትል አውቶቡሶች ተመርተው አልቀዋል፤ አምስት ሹፌሮችና አንድ መካኒክ ስልጠና ወስደዋል፤የመጨረሻ ክፍያ በመፈጸም መኪኖቹን ለመረከብ በሂደት ላይ እንገኛለን፡፡
- ለአካዳሚክና አስተዳደር ሠራተኞች የቤት አውቶሞቢል በዱቤ ግዥ ለማመቻቸት ኮሚቴው የጥናትና ምርምር ሥራን አከናውኖ ለበላይ አመራር ገለፃ ለማድረግ በሂደት ላይ ነው፡፡
- የኪቶ ፉርዲሳ ሁለገብ ልማት ኢንተርፕራይዝ የዶሮና አሳማ ቤት ለማስፋፋት ጨረታ አሸናፊው መሬት ቁፋሮና የመሰረት ሥራ በመስራት ላይ ነው
- የከብት ርባታ ቤት ፍሳሽ ማስወገድና የጥገና ስራ ተለይቶ የጨረታ ሂደት ውስጥ ለመግባት ሁኔታዎች እየተመቻቹ ነው፡፡
- 207 የትራክተር ጋሪ የከብቶች መኖ ሳር ታጭዶ በጥቅም ላይ እየዋለ ይገኛል፤

- 10,000 ችግኝ ዴሽ ሳር ተገዝቶ ተተክሏል፤
- 0.5 ሜትር ኪዩብ የከብቶች መኖ ሳይሌጅ ከበቆሎ አገዳ ተዘጋጅቶ ጥቅም ላይ ለማዋል ሂደት ላይ ይገኛል፤
- 12 የተዳቀሉ ጊደሮች ከወለጋ ዩኒቨርሲቲ ተገዝተዋል
- የ3 ሄክታር ሙዝ፣ አቮካዶና ማንጎ ዛፎች እንክብካቤ እየተደረገላቸው ነው፤
- በሩብ አመቱ 50,187 ሊትር ወተት ለማሰራጨት ታቅዶ 42,420 ሊትር ተሰራጭቷል፤ ይህም ከዕቅዱ 84.82% ነው
- በሩብ ዓመቱ 225,000 እንቁላል ለመሸጥ የታቀደ ሲሆን 232,811 በመሸጥ ከዕቅዱ 103.47% ተከናውኗል፡፡
- የሠራተኛ መዝናኛ ክበብ ቀልጣፋና ምቹ አገልግሎት እንዲሰጥ መጠገን የሚገባቸው ዕቃዎች ተጠግነዋል፤ ማብሰያ ቤት እድሳት በሂደት ላይ ነው፤
- የቁሳቁሳ ማምረቻና ጥገና ኢንተርፕራይዝ ያለቁ ምርቶችን ማከማቻ ስራ ለማስጀመር ዲዛይንና ዝርዝር ሰነድ ተዘጋጅቶ ለማፅደቅ በሂደት ላይ ነን፤
- የቁሳቁስ ማምረቻና ጥገና ኢንተርፕራይዝ የሚያመርታቸውን አነስተኛ ምርቶች ለሰራተኛ በሽያጭ ለማቅረብ የቀድሞውን ቡክ ሴንተር በማሳደስ ዝግጁ ተደርጎ ዕቃዎች በመገዛት ላይ ናቸው፡፡
- አዲሱን ሞዴል ፋርማሲ በአዲሱ ሪፈራል ሆስፒታል በመስራት ለአገልግሎት ዝግጁ ለማድረግ ጥቂት የማጠቃለያ ስራዎች ብቻ ቀርቷል
- የጅምላ የመድሃኒትና ሬኤጀንቶችን ማከፋፈያ ለማቋቋም የፈቃድ ማስረጃ ለማውጣት ከኢትዮጵያ የመድሃኒት ፈንድ ቁጥጥር ባለስልጣን ጋር ምክክር እየተደረገ ነው፡፡ የማመልከቻ ቅፅ ተሞልቶ ስራው በሂደት ላይ ይገኛል፡፡

## ፕሮግራም ሁለት. የአካዳሚክ ልዕቀት

ጅማ ዩኒቨርሲቲ የላቀ መማር/ ማስተማር ስራን ዕውን ለማድረግ፣ ፈጠራና ጥበብን ለማጎልበትና ከፍተኛ የትምህርት ብቃትን ዕውን ለማድረግ ስርዓተ ትምህርቶችን፣ ስትራተጂዎችና የምዘና ስርዓት ቀርጾ ስራ ላይ አውሏል፡፡ የመማር/ ማስተማር ስራ ስኬታማ ለማድረግ ለመምህራን፣ ተመራማሪዎች፣ ተማሪዎችና ሠራተኞች ምቹና ተስማሚ አካባቢ ለመፍጠርና ምሁራዊ ጥበቦችና የአካዳሚክ ነፃነትን ለመንከበካብና ለማሳደግ በርካታ ስራዎች በመሰራት ላይ ናቸው፡፡ መጪውን ጊዜ የተሻለ ለማድረግና የማህበረሰቡን ፍላጎት ለማሟላት ሙያዊ ስብጥርን ለማቀናጀትና የላቀ ዕውቀትን ለማመንጨት ብርቱ ጥረት እየተደረገ ነው፡፡

በዚህ ፕሮግራም ስር በዝግጅት ምዕራፍ ከመማር ማስተማር ተያይዞ የተሰሩ ስራዎች በዝርዝር የሚቀርቡበት ክፍል ነው፡፡ ይህን ዕውን ለማድረግ የተመረጡ ስትራተጂያዊ ስልቶች ስራ ላይ ውለዋል፡፡ በዚህም መሰረት የተቋሙን የመቀበል አቅም ለማሳደግ፣ ለሴቶች፣ ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎችና በማደግ ላይ ላሉ ክልሎች ድጋፍ ለመስጠትና የትምህርት ግብዓቶችን ለማሳደግ፣ ኢለርኒንግ ፕሮግራሞችን ለማስፋፋት፣ ሴቶችና ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ተማሪዎች ነፃ ትምህርት ዕድል ለማመቻቸት ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ ከዚህ አንፃር በዚህ የሩብ ዓመት ውስጥ የተከናወኑ ስራዎች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### ዓላማ 2.1. የከፍተኛ ትምህርትን ተደራሽነትና ፍትሐዊነት ለማሳደግ የተከናወኑ ስራዎች

**ሠንጠረዥ 13.** የተማሪዎች ቁጥር

| ቁልፍ የአፈፃፀም ማሳያዎች | መለኪያ | የዓመቱ ዕቅድ | የ1ኛ ሩብ ዓመት | | የሩብ ዓመት አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | |
| በዚህ ዓመት የተመደቡ መደበኛ ቅድመምረቃ | | | | | |
| በኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ ዘርፍ | ቁጥር | 4838 | 4838 | 100 | 100 |
| በተፈጥሮ ቀመር ሳይንስ ኮሌጅ | ቁጥር | 6269 | 6269 | 100 | 100 |
| በሕክምና ጤና ሳይንስ ዘርፍ | ቁጥር | 751 | 751 | 100 | 100 |
| በግብርና ዘርፍ | ቁጥር | 3041 | 3041 | 100 | 100 |
| በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ዘርፍ | ቁጥር | 1209 | 1209 | 100 | 100 |
| በህብረተሰብ ሳይንስና ሂውማኒቲስ ዘርፍ | ቁጥር | 1135 | 1135 | 100 | 100 |
| የመማሪያ ክፍል ብዛት | ቁጥር | 279 | 279 | 100 | 100 |
| ቅድመ ምረቃ ተማሪ/መደበኛ | ቁጥር | 19054 | 19054 | 100 | 100 |
| ሁለተኛ ዲግሪ ተማሪ/መደበኛ | ቁጥር | 1779 | 1779 | 100 | 100 |
| ሶስተኛ ዲግሪ ተማሪ/መደበኛ | ቁጥር | 206 | 206 | 100 | 100 |
| **ቅድመ ምረቃ/ተማሪ ተከታታይ ትምህርት** | | | | | |
| - ማታ | ቁጥር | 3084 | 3084 | 100 | 100 |
| - ክረምት | ቁጥር | 6864 | 6864 | 100 | 100 |
| - የርቀት ትምህርት | ቁጥር | 3267 | 3267 | 100 | 100 |
| **ድህረምረቃ ተማሪ/ተከታተይ ትምህርት** | ቁጥር | | | | |
| - ማታ | ቁጥር | 2290 | 2290 | 100 | 100 |
| - ክረምት | ቁጥር | 894 | 894 | 100 | 100 |
| - የርቀት ትምህርት | ቁጥር | 2642 | 2642 | 100 | |
| - PDDT | ቁጥር | 2286 | 2286 | 100 | |
| የዶክቶራል ስልጠና መመሪያውን ማስፀደቀቅና ማሳተም | ቁጥር | 1 | 1 | 1 | 100 |
| በከተሞችና በአጎራባች ሀገሮች የድህረምረቃ መርሃ ግብር መጀመርና ማጠናከር (Lucy 3, ABH 2, Hargeisa 2) | ካምፓስ ቁጥር | 7 | 7 | 4 | 57 |

**መደበኛ ተማሪዎች (ቅድመ ምረቃና ድህረምረቃ)**

- ለተማሪዎች መማሪያ ክፍል፤ ቤተመፅሃፍት፤ ላበራቶሪ፤ ኮምፒውተር ማዕከላትና ለመማር ማስተማር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያላቸው አገልግሎት ማስጫ ማዕከላትን የማጠናከር፣ የማደስና የማዘጋጀት ስራ ተከናውኗል፡
- የ2010 ዓ.ም አካዳሚክ ካላንደር ፀድቆ ለኮሌጆች፣ ትምህርት ክፍሎችና መምህራን እንዲደርስ ተደርጓል፤ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ዝግጅትና ኮርስ ድልድል ተከናውኗል።
- አዲስ ለገቡ ተማሪዎች ስለ ዩኒቨርስቲው ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፤ ተማሪዎቹ የሚፈልጉትን የትምህርት መስክ በፍላጎታቸው መርጠዋል፤ የትራንስፖርት መጨናነቅን ለመቅረፍ ዩኒቨርስቲው የራሱን ተሽከርካሪ አዲስ አባባ በመላክ ተማሪዎቹን ከእንግልትና አስፈላጊ ወጪ አድኗል
- የነባርና አዲስ ተማሪዎች ቅበላና ምዝገባ ተከናውኗል፣ የፈርስት ዴይ ፈርስት ክላስ መርሃግብር ተከናውኗል፣ በሰላማዊ የመማር ማስተማር ሂደት ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር (ከተማ መስተዳደር፣ ደህንነት አካላትና ከዩኒቨርሲቲዉ አመራር ጋር ምክክር ተደርጓል)
- በሁለተኛ ዲግሪ መደበኛ ኘሮግራም ፈተና ያለፉ ተማሪዎችን በመለየት የመደበኛው ኘሮግራም ትምህርት እየጀመሩ ነው።
- አዲስ በሚከፈቱ PhD ኘሮግራሞች የሶስተኛ ዲግሪ ተማሪዎችን ተቀብለናል፣ ሁለተኛ ዲግሪ ተማሪዎች ለምርምር ስራ ርዕስ እንዲያዘጋጁ፣ የምርምር ርዕሳቸውንና አድቫይዘር በሰዓቱ መርጠው ኘሮፖዛላቸውን እንዲያቀርቡ ተደርጓል
- የነባር ተማሪዎች ምዝገባና ስልጠና ተካሂዷል፣ የክረምት ነባርና አዲስ ተማሪዎች ምዝገባ ተካሂዷል፣
- አዲስ ለተቀጠሩ መምህራን ኮምፒውተርና ኔትዎርክ እንዲያገኙ ተደርጓል
- የነባርና አዲስ ተማሪዎች ጥሪ በቴሌቪዥንና በሬዲዬ እንዲነገር ተደርጓል
- የድህረ ምረቃ ተማሪዎች አመልካቾች በሚዲያ ተነግሯል የ2010 የድህረ ምረቃ ተማሪዎች ምልመላ ተካሂዷል

**መደበኛና ተከታታይ ትምህርት መርሃ ግብር**

- በ2010 የትምህርት ዘመን 32,269 ተማሪዎች በቅድመ-ምረቃና 8112 ተማሪዎች በሁለተኛ ድህረ መርሃ ግብር በትምህርት ገበታ ላይ ተገኝተዋል። ከነዚህ መካከል 26,869 ወንዶች ሲሆኑ ቀሪው 13,718 ሴቶች ናቸው።

**የፆታ ስብጥር**

- የወንድና ሴት መምህራን የፆታ ስብጥር 85:15 ሲሆን የወንድና ሴት ተማሪዎች የፆታ ስብጥር ደግሞ 66:34 ነው። ይሁን እንጂ በአስተዳደርና ድጋፍ ሰጪ ዘርፍ የሴቶች ድርሻ በጣም የተሻለ ሆኖ ታይቷል። በመሆኑም ካሉን 6016 ሰራተኞች መካከል 64 ከመቶው ሴቶች ናቸው ፤ ይህም ከአምናው የ54:46 የወንዶችና ሴቶች ስብጥር ጋር ሲወዳደር በጣም የሴቶች ቁጥር በጣም መሻሻሉን ያሳያል።

**ልዩ ፍላጎት ላላቸው፣ ለታዳጊ ክልልና ለሴት ተማሪዎች የተደረገ ድጋፍ**

- ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ምቹ ቤተመፅሃፍት ተዘጋጅቷል፤ ጀውስና NDVM የሚባሉና በአማርኛ ሊያስጠቅሙ የሚችሉ ሶፍትዌሮች አገልግሎት ላይ ዉሏል
- ቀደም ሲል ሲሰራበት የነበረው የቱቶሪያል አገልግሎት ውጤት ግምገማ በጥናት እስኪረጋገጥ ድረስ እየታየ ያለውን የሴት ተማሪዎች መጠነ ማቋረጥና መድገም ለመቅረፍ የቱቶሪያል ሪፎርምና ማዋቀር ስራ ተሰርቷል
- ለሴት መምህራን ቅድሚያ በመስጠት ለ135 ሴት መምህራን የመኖሪያ ቤት እንዲያገኙ ተደርጓል፣ ህፃናት ላላቸው ሴት መምህራን አመቺ የስራ አካባቢ ለመፍጠርም በዋና ግቢና ቴክኖሎጂ ካምፓሶች የ Day Care አገልግሎት ለመስጠት ዝግጅት እየተደረገ ነው
- በሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ በተዘጋጀ ማሰልጠኛ ማኑዋል መሠረት ስልጠና የወሰዱ መምህራን ተማሪዎችን አሰልጥነዋል። በትምህርት ክፍል አመዳደብ ለሴት ተማሪዎች ቅድሚያ እንዲሰጥ ተደርጓል።
- የኤች አይ ቪ/ ኤድስ ተግዳሮትን ለመገዳደር የሁሉንም ክፍሎች፣ ፕሮግራሞችና ባለድርሻዎች ተሳትፎ በማሳለጥና ማህበረሰቡን በማንቀሳቀስ የግንዛቤ ፈጠራ ዘመቻ ተደርጓል፤ ኤች አይ ቪ/ ኤድስን ለመታገል የሚያስችል የተቀናጀ የተማሪዎች አገልግሎት ማዕቀፍ ተዘጋጅቷል፤ ጉዳዩን ሊያግዙና ሊያሳልጡ የሚችሉ የህትመትና ዲጂታል የብዙሃን መገናኛ ዘዴዎች/ *ዳና መፅሔት፣ በራሪ ፅሁፎች፣ የማህበረሰብ ሬዲዮ፣ የዲጂታል መገናኛ ዘዴዎችና አቻ ለአቻ ውይይቶች/* በመጠቀም መረጃ ተሰራጭቷል፤ ማህበራዊና

ተያያዥ የጤና ምክር አገልግሎቶች ተሰጥቷል፡፡ የተዘጋጁት ፓናል ውይይቶች ኤች አይ ቪ/ ኤድስን ለመግታት/ ለመቀነስ በብሔራዊ ደረጃ ከተደረጉ ጥረቶችና ስኬት መካከል አንዱ ሆኗል፡፡ በተመሳሳይም በአቻ ለአቻ የአሰልጣኞች ስልጠና 10 ሰልጣኞች ተሳትፈዋል፣ የስልጠና ማቴሪያሎችን አዘጋጅቶ ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብና ለጅማ ከተማ ቀበሌዎች ተሰራጭቷል፣ 76 ሰልጣኞች በአጋላጭ የፆታ ግኑኝነት ላይ ለዩኒቨርሲቲው ፖሊሶች፣ ፕሮክተሮች፣ ፅዳት ሰራተኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ከጊንጆ ቀበሌ አመራርና 38 የማህበረሰብ ተወካዮች ጋር የጋራ ውይይት ተደርጓል፡፡

**የመምህራንን አካዳሚያዊ ደረጃ ማሳደግ**

- ፍላጎት ላይ መሰረት ያደረገ የመምህራን ምልመላና ቅጥር ከሃገር ውስጥና አገር ውጭ ተከናውኗል
- የሁለተኛና ሶስተኛ ዲግሪ የመምህራን ትምህርት ዕድል ቅድሚያ ትኩረት ለሚሹ ትምህርት መስኮች ተመቻችቷል ፡፡
- የመምህራንን አቅም ለማጎልበት (HDP፤ በምርምር፣ አካዳሚክ ፕሮግራም ሪቪው፣ ስነ ፆታ፤ SPSSና GIS ስልጠና ተሰጥቷል
- በ2010 ለተቀጠሩ አዲስ አካዳሚክና አስተዳደር ሰራተኞች ስለዩኒቨርስቲው የማስተዋወቂያ ስልጠና ተሰጥቷል፣
- ከሁሉም የዩኒቨርሲቲዉ ማህበረሰብ ጋር ስለ 2009 ዓ.ም. ዕቅድ ክንውንና ስለታዩ በጎ ጎኖችና ክፍተቶች ውይይት ተደርጓል

**ተማሪዎችን በኢንተርንሺፕ፣ ፕራክቲከምና ፕሮፌሽናል ፕራክቲስ ማሰማራት**

- በኢንተርንሺፕ፣ ፕራክቲከምና ፕሮፌሽናል ፕራክቲስ ለሚሰማሩ ተማሪዎችና ሱፐርቫይዘሮች ቅድመ ዝግጅት ተደርጓል፣ ለክረምትና ነባር ተማሪዎች በኢንተርንሽፕ፤ ፕራክቲከምና ፕሮፌሽናል ፕራክቲስ ስራዎች ተሰርተዋል፡

**ትምህርት የመጨረስ ምጣኔ**

- በዝግጅት ሪፖርት ማቅረቢያ ወቅቱ የተማሪዎች የመጨረስ ምጣኔ 93.8 ከመቶ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡

**ዓላማ 2.2. የከፍተኛ ትምህርት ጥራትና አግባብነትን ለማሻሻል የተከናወኑ ስራዎች**

የከፍተኛ ትምህርት ጥራትና አግባብነትን ለማሻሻል በተቀረፁ ስትራተጂያዊ ስልቶች ላይ በርካታ ስራዎችን በማከናወን በገበያ ተፈላጊና ተወዳዳሪ ምሩቃንን ለማፍራት ብርቱ ጥረት ተደርጓል፣ ደረጃና ጥራታቸውን የጠበቁ የትምህርት መስጫ መሳሪያዎች፣ የስልጠና ሞጁሎችና ድረገፅ ማስተማሪያ ግብዓቶች ተዘጋጅተዋል፣ የመምህራንን የትምህርት ደረጃ ስብጥርን ለማሻሻል ደረጃውን የጠበቀ የቤተመፃህፍት አገልግሎት ለመስጠትና ከፍተኛ ጥራት ያለው የኮምፒውተርና ድረገፅ መሰረተ ልማቶችን ለማደራጀት የተከናወኑ ስራዎች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 14. የከፍተኛ ትምህርት ጥራትና አግባብነትን ለማሻሻል የተከናወኑ ስራዎች

| ቁልፍ የአፈፃፀም ማሳያዎች | መለኪያ | የዓመቱ ዕቅድ | የ1ኛ ሩብ ዓመት | | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | |
| የተገመገመ M.Sc. MA/ MPH/ ፕሮግራም | ቁጥር | 4 | 2 | 2 | 100 |
| የተገዙ መፃህፍት | ቁጥር | 4000 | 4000 | 0 | 0 |
| በግዥና ስጦታ የተሰበሰቡ መጽሀፍት | ቁጥር | 1635 | 408 | 0 | 0 |
| በግዥ የተገኙ መጽሄቶችና ጆርናሎች | ቁጥር | 3712 | 928 | 836 | 90 |
| በኦቶሜሽን ዳታ ኢንትሪ የገቡ መጽሀፍት | ቁጥር | 6735 | 1684 | 1227 | 73 |
| ሜታ ዳታ ኢዲቲንግ | ቁጥር | 3400 | 850 | 87 | 10 |
| ካርድ ካታሎግ የተሰራላቸዉ መጽሀፍት | በርዕስ | 1347 | 336 | 180 | 53 |
| የመጽሀፍት ሌብሎችና ባርኮዶች | ቁጥር | 6735 | 1684 | 895 | 53 |
| ለቤተመፅሃፍት የተሰራጩ መፅሀፍት | ቁጥር | 6735 | 1684 | 896 | 53 |
| ለቢሮዎች የተሰራጩ ቻዜጦችና መፅሃፍቶች | ቁጥር | 36003 | 9001 | 8975 | 99 |
| ፎቶኮፒ ተደርገዉ አገልግሎት የዋሉ መፅሀፍት | ገጽ ብዛት | 160080 | 40020 | 28010 | 70 |
| ዲጅታል ላይብረሪ ሲስተም የገቡ መፅሃፍት | ቁጥር | 9000 | 1000 | 804 | 80.4 |
| ጥናትና ምርምር ውጤቶች ሪፓዚቶሪ ዲጅታል ዳታ ቤዝ ማስገባት | ቁጥር | 3000 | 1000 | 250 | 25 |
| የተሰበሰቡ ጥናትና ምርምር ውጤቶች (ሀርድ ኮፒ) | ቁጥር | 3000 | 1000 | 200 | 20 |
| ለኮምፒዩተሮች ተያያዥነት ላላቸዉ  ማቴሪያሎች ጥገና ማድረግ | ቁጥር | 300 | 80 | 69 | 86.25 |
| የኔትወርክ ኢንስታሌሽን (ዝርጋታ) ና የዩቲፒ ኬብል ክሪንፒንግ | ቁጥር | 300 | 75 | 95 | 126.66 |
| በአገልግሎት ምክንያት ያረጁ ኮምፒዩተሮችን ማስወገድ | ቁጥር | 500 | 500 | 450 | 90 |
| ኤግዚብሽን ማካሄድና መሰተፍ | ቁጥር | 6 | 3 | 3 | 100 |
| በዋናው ግቢና ቴክኖሎጅ ኢንስቲትዩት የድህረ ምረቃ ቤተመፃህፍት፣ በቴክኖሎጅ ኢንስቲቲዩት የሴቶች ቤተመፃህፍት መክፈት | ቁጥር | 3 | 2 | 2 | 100 |

**በገበያ ተፈላጊና ተወዳዳሪ ምሩቃን ማፍራት፣ ትምህርት መሳሪያዎች ዝግጅትና ስርጭት**

- የአዲስ መምህራን ቅጥር ተካሂዷል
- የመምህራን ኮርስ ምደባ በወቅቱ ተከናውኗል
- Re-exam ያለባቸው ተማሪዎች ተለይተው የፈተና ኘሮግራም እየተዘጋጀ ነው
- Add and Drop ያለባቸው ተማሪዎች ተለይተው ጉዳያቸው እየታየ ይገኛል፡፡
- ከ1ኛ -3ኛ ዓመት ላሉ ተማሪዎች የacademic and social advisor በቅርቡ የመመደብ ዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡
- ለርቀት ተማሪዎች የቱቶሪያል/ የፈተናና ሌሎች ተያያዥ ሥራዎች ተሠርተዋል
- ያረጁና ከጥቅም ውጭ የሆኑ ሞጁሎችን በመለየት እንደገና እንዲታደሱ ለትምህርት ክፍሎቸ እንዲዘጋጁ ማድረግ ተችሏል
- በአስተዳደር ሰራተኞች በቲም ወርክ ተደራጅተው እየተሰራበት ይገኛል፡፡
- የላቦራቶሪ ክፍሎችና ማቴሪያሎች ማዘጋጀት ሂደቱ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል
- መምህራንና ተማሪዎች ክፈለ-ጊዜዎቻቸውን ጠብቀው መግባታቸውን ክትትል ተደርጓል
- የተማሪዎች ውጤት በወቅቱ እንዲገባ፣በሰዓቱ እንዲያዩና በወቅቱ እንዲመዘገቡ አድ/ድሮኘ፣ ሜካአኘና ሪ-ኤግዛም በታቀደለው ጊዜ እንዲከናወን ተደርጓል
- አዲስ ለተቀጠሩና induction and HDP ያልወሰዱ መምህራን ስልጠና እንዲዘጋጅ የማሳወቅ ስራ ተከናውኗል፡፡
- የፈተና ኘሮግራም ማውጣት መምህራንን መደልደልና ፈተናው በተገቢው ኘሮግራም መስጠት ተችሏል
- ለየትምህርት ክፍሎች የሚያስፈልጉ መጽሐፍት ፍላጎቶችን ለቤተ መጽሐፍት አሳውቋል
- ለተግባር ልምምድ የሚወጡ ተማሪዎች አግባብነት ያላቸው በታዎች ተለይቷል

- የትምህርት ጥራት ማስጠበቂያና ማስተማር ክህሎት ማዳበሪያ ርስ-በርስ ውይይት ተዘጋጅቷል፤ የክህሎት ማዳበርያ ስልጠና ተሰጥቷል
- የቤተሙከራ አቅም ለማሳደግ ጥረት ተደርጓል፤ የላበራቶሪ ተቆጣጣሪና ቴክኒክ ረዳቶችን እንዲቀጠሩ ተጠይቋል፡፡

**የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስር**

- ለ23 የ2009 ዓ.ም ተመራቂ ተማሪዎች ባበረከቱት የላቀ የቴክኖሎጂ ሽግግር ግብአት ማበረታቻ ነፃ የትምህርት ዕድል ተሰጥቷል
- ለ8ኛ ሀገር አቀፍ የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ሽልማት ውድድር ከላክናቸው ሰባት ስራዎች አምስቱ ለሽልማት መመረጣቸው ተገልፆልናል
- ከኦሮሚያ የኢንዱስትሪ ፓርክ ልማት ማዕከል ጋር በጋራ ለመስራት የውይይት መድረክ ተዘጋጀቶ ውይይት ተደርጓል
- ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ጋር ባለው የስራ ትብብር መሰረት ለአንድ የጅማ ፖሊቴክኒክ አሰልጣኝ በማኑፋክቸሪንግ ኢንጂነሪንግ የሁለተኛ ዲግሪ የትምህርት ዕድል ተሰጥቷል፡፡
- የኢንተርንሺፕ አተገባበር ያበረከተው አስተዋፅኦና ተፅዕኖ የጥናት ዳሰሳ ከGIZ፣ ባህርዳርና አ.አ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር የጥናት መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በጥናቱ ላይ የጅማ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የምዕራብና ደቡብ ምዕራብ ቀጠና አስተባባሪ ነበር
- በህግና ገቨርናንስ ኮሌጅ ከ4 ተቋማት ጋር በምርምርና ድ/ምረቃ ትምህርት ዘርፍ ግንኙነቶችን ለመመስረት ውይይት ተደርጓል
- ከ GIZ ጋር በመተባበር የቴክኖሎጂ ሽግግር ያተገባበር ሂደት መመሪያ ተዘጋጅቶ የመጀመሪያ ፈርስት ድራፍት ተጠናቋል፡፡
- ከኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማናጅመንት ጋር በመተባበር በጋራ የሚሰራ የትብብር የምርምር ስራ ተጀምሯል፡፡

**የቤተመፃህፍት አገልግሎትና የድረገፅ መሰረተ ልማቶች**

- መፅሃፍት በኦቶሜሽን ዳታ ኢንትሪ ገብተዋል /OPAC ን abcd.ju.edu.et/iah መጠቀም ይቻላል/ ፣ ሜታ ዳታ ኢዲቲንግ ተደርጓል፣ ካርድ ካታሎግ፣ ሌብሎችና ባር-ኮዶች ተሰርቷል፣ መፅሃፍት ለቤተመፅሃፍት ተሰራጭተዋል፣ መፅሃፍት ወደ ዲጅታል ላይብረሪ ሲስተም ገብተዋል፣ በአጠቃላይ 20000 መጽሀፍት አሉ library.ju.edu.et:8080
- በኢሜይል መረጃ የመስጠት አገልግሎት አዲስ Online reference & reserving ተጀምሯል
- 250 GB ዲጂታል ላይብረሪ ሶፍት ኮፒ መፅሃፍቶች ተሰብስበዋል፡፡ /በአጠቃላይ ከ4 ቴራ ባይት በላይ ሶፍት ኮፒ መፅሃፍቶች አሉ
- A Guide to Electronic Libraries on Internet የሚል አጠቃቀም መመሪያ ለድህረምረቃ ተማሪዎችና መምህራን ተሰራጭቷል
- ታዋቂ አለማቀፍ ጆርናሎች ለተጠቃሚ ቀርቧል www.ju.edu.et/library/ www.ju.edu.et/library/node/102
- የጥናትና ምርምር ውጤቶች ሪፓዚቶሪ ዲጅታል ዳታ ቤዝ ገብተዋል፣ ኮምፒዩተሮችና ኮምፒዩተር ነክ ማቴሪያሎች ጥገና ተደርጓል

## ዓላማ 2.3. ኢንተርፕረነራል ትምህርትና የስራ ፈጠራ ክህሎትን ማሳደግ

የሥራ ፈጠራና ኢንተርፕረነርሺፕ አመለካከት ወደተማሪዎች ሌሎች የማህበረሰቡ አባላት እንዲሰርፅ በአገራችን የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ከተቀመጡ መሠረታዊ አቅጣጫዎች አንዱ ሲሆን ዘርፉም በሥራ ገበያ ተወዳድሮ መቀጠርን ሳይሆን የራስን ዕውቅትና አቅም በመጠቀም ራስን የመቅጠር አቅጣጫ በመከተል ሥራ አጥነትና ድህነት በመቅረፍ ሰፊ የሥራ ዕድል ይፈጥራል፡፡ በዚህ የአመለካከትና የአሰራር ለውጥ ተጠቃሚዎች የሚያገኙትን ድጋፍ፣ ምክርና አገልግሎት ለውጤት እንዲያበቁና በገበያ ላይ ብቁ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ እያገዘ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ጅማ ዩኒቨርሲቲ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ስራ ፈጠራ ለማስፋፋትና የዕውቅት፣ ክህሎትና አመለካከት በገበያ ፍላጎት የተመሠረተ የሥልጠና ስርዓት ዘርግቷል፣ የምክር አገልግሎት ሽፋን ለማሳደግና የመረጃ አያያዝ ስርዓት ለማጠናከር፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሠራርን ለማጠናከርና ትስስር ለመፍጠር በርካታ ስራዎች እንደሚሰሩ ይጠበቃል፡፡

- የጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ፅዳት ስራን ለስራ አጥ ከተማ ወጣቶችና ሴቶች ተደራጅተው በኮንትራት እንዲሰሩ (outsoursing) ተጠንቶ በጨረታ ሂደት ላይ ይገኛል ፡፡
- ለጅማ ከተማ ወጣቶችና ሴቶች ስራ ዕድል ለመፍጠር ከጅማ ዞን አስተዳደር፣ ጅማ ከተማ ምክር ቤት፣ ከጅማ ዞንና ጅማ ከተማ የስራ ፈጠራና ምግብ ዋስትና መ/ቤቶችና የጅማከተማ ሴክተር መ/ቤቶች ጋር በመተባበር ለጅማ ዩኒቨርሲቲ ምግብና የምግብ ግብዓት እንዲሁም የግንባታ ቁሰቁሶች ለማቅረብ ለተደራጁ ወጣቶችና ሴቶች ስራውን በኮንትራት ለመስጠት (outsoursing) ለማድረግ ከላይ የተጠቀሱትን ዕቀዋች ከሚየቀርቡ ድርጅቶች ጋር ስምምነት ተደርጓል
- ለጎዳና ተዳዳሪነት ለተጋለጡ ህፃናት የገቢ ማስገኛ ማዕከላት ተደራጅቷል
- አካዳሚክ ውጤታቸው ዝቅተኛ ለሆኑና ለተባረሩ 242 ሴት ተማሪዎች ተግባራዊ ሙያ ስልጠና ተሰጥቷል
- የተቀናጀ የዶሮና አሳ ለምግብ ዋስትናና የገበሬን ኑሮ ለማሻሻል ለቤተሰቦች የስራ ዕድል ተፈጥሯል፣ ገቢያቸውን አሻሽሏል
- ለአርሶአደሩ አማራጭ ገቢ ምንጭ ለመመስረት በገበሬ ማሳ የንብ ማነቢያ ጣቢያዎች ተመስርተዋል፣ ወጣቶችና ችግረኞች በገቢ ማስገኛ ተሳተፈዋል፣ ወጣቶችና አባወራዎች ስልጠና ወስደዋል

## ፕሮግራም 3. ጥናት ምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር

ጅማ ዩኒቨርሲቲ መምህራንና ተመራማሪዎችና ድህረምረቃ ተማሪዎች አዳዲስ ዕውቀትና ክህሎት ማንጨት የሚያስችል አመቺ ሁኔታዎች ለመፍጠር ይተጋል። ይህንኑ በማረጋገጥ ለአገሪቱ ቀዳሚ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ካባቢያዊ ጠቀሜታ ባላቸውና አዎንታዊ ተፅዕኖ ማምጣት በሚያስችሉ የትኩረት መስኮች ግንባር ቀደም ሚና ለመጫወት በሚከተሉት ዒላማዎች ላይ በትኩረት ሰርቷል። በዚህ ፕሮግራም ስር ዩኒቨርሲቲዉ ባሳለፍነዉ ሩብ አመት /ዝግጅት ምዕራፍ / በጥናትና ምርምር እንዲሁም በቴክኖሎጅ ሽግግር የስራቸውን ስራዎች አንድ በአንድ በዝርዝር የሚቀርብበት ክፍል ነዉ። በዚሁ መሠረት ምንም እንኳን በዝግጅት ምዕራፍ ዋናዋና ተግባራቶች ባይሰሩም ለዋና ዋና ተግባራቶች ሂደት አመቺነት የተሰሩ ስራዎች ይቀርባሉ።

### ዓላማ 3.1. ደረጃውን የጠበቀ ምርምር፣ ፈጠራና ግኝትን የሚያበረታታ ምቹ ሁኔታ መገንባት

**ሠንጠረዠ 15. ጥናትና ምርምርና የቴክኖሎጂ ሽግግር**

| የአፈፃፀም መለኪያ | መለኪያ | የ2010 ዓ.ም ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | የዓመቱ ዕቅድ | የ1ኛ ሩብ ዓመት ዕቅድ | የ1ኛ ሩብ ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም | |
| | | | | በቁጥር | በመቶኛ |
| በድህረ ምረቃ ተማሪዎችና መምህራን የሚሰሩ ችግር ፈቺ ምርምሮች | ቁጥር | 410 | 102 | 92 | 90 |
| ከውጪ ምንጮች በተገኙ ግራንቶች የሚከናወኑ ምርምሮች ብዛት | ቁጥር | 40 | 13 | 13 | 100 |
| ከአጋር ድርጅቶች ጋር በጋራ የሚሰሩ ምርምሮች | ቁጥር | 24 | 9 | 9 | 100 |
| በአለምአቀፍና ሀገር አቀፍ ጆርናሎች የሚታተሙ ምርምር ውጤቶች | ቁጥር | 450 | 110 | 92 | 84 |
| የሚወጡ የፖሊሲ ብርፎች ብዛት | ቁጥር | 10 | 2 | 1 | 50 |
| የሚካሄዱ የኮንሰልታንሲ ስራዎች ብዛት | ቁጥር | 16 | 4 | 2 | 50 |
| የተሰጡ የአቅም ማጎልበቻ አጫጭር ስልጠናዎች፡ ወርክሾፖች | ቁጥር | 30 | 3 | 2 | 67 |
| የሚዘጋጁ ፐብሊክ ሌክቸሮች ብዛት | ቁጥር | 12 | 3 | 0 | 0 |
| የሚቋቋሙ ማእከላዊ (Core) ላቦራቶሪ ራቶርዎች | ቁጥር | 1 | 1 | 0 | 0 |
| ዳታ ቤዝ ማቋቋም | ቁጥር | 4 | 1 | 0 | 0 |
| የተለያዩ ሰታትስትካል ሶፍት ዌሮችን መግዛት | ቁጥር | 4 | 1 | 0 | 0 |
| የምርምር ስልጠና ማዕከላትን ማደራጀት | ቁጥር | 1 | 0 | 0 | 0 |
| የምርምር ማዕከላትን/ሴንተሮችን ማደራጀት | ቁጥር | 2 | 0 | 0 | 0 |
| አለም አቀፍ/ ሀገር አቀፍ የምርምር ኮንፈረንሶችን ማዘጋጀት | ቁጥር | 5 | 1 | 0 | 0 |
| በዩኒቨርሲቲው የሚታታሙ ጆርናሎች አለምአቀፍ ስታንዳርድ (Online System) እንዲኖራቸው ማድረግ | ቁጥር | 1 | 0 | 0 | 0 |
| ወደ ማህበረሰቡ የሚሸጋገሩ ቴክኖሎጂዎችን ማሸጋገር | ቁጥር | 10 | 2 | 2 | 100 |
| የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትር ትስስር መፍጠር | ቁጥር | 10 | 4 | 4 | 100 |
| የቴክኖሎጂ ኢንኩቤሽንና ፓርኮች መፍጠር / በሂደት ላይ ነው | ቁጥር | 1 | 0 | 0 | 0 |
| ቴክኖሎጂ ውጤት ማሳያ/ ማሰራጫ ስልት ዝግጅት/ሂደት ላይ ነው | ቁጥር | 1 | 0 | 0 | 0 |
| የቴክኖሎጂ ሽግግር መመርያን መከለስ/ማዘጋጀት /በሂደት ላይ ነው | ቁጥር | 1 | 0 | 0 | 0 |
| በቴክኖሎጂ ሽግግር የሚሳተፉ መምህራንና ተማሪዎች መጨመሩ | ቁጥር | 20 | 5 | 0 | 0 |
| ከTVET ጋር ግንኙነትና ትስስር መፍጠር /ውል በመጠናቀቅ ላይ ነው | ቁጥር | 1 | 0 | 0 | 0 |
| የባለድርሻ አካላት ፎረም ማቋቋም /በሂደት ላይ | ቁጥር | 2 | 1 | 0 | 0 |
| የማህበረሰብ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ብዛት/ ተዘጋጅቶ ተጠናቀል | ቁጥር | 800 | 570 | 580 | 98.3 |
| የማህበረሰብ አገልግሎት መመርያን መከለስ/ማዘጋጀት | ቁጥር | 1 | 1 | 1 | 100 |
| ቁልፍ የማህበረሰብ ችግሮችን መለየትና ምርምር ማካሄድ /ሂደት ላይ | ቁጥር | 10 | 2 | 0 | 0 |
| በማህበረሰቡ ሰብአዊ እንቅስቃሴዎችን ማከናወን/ በሂደት ላይ ነው | ቁጥር | 1 | 0 | 0 | |

**የጥናትና ምርምር አቅም ግንባታ**

- አሁን ስራ ላይ ያሉ 430 ረዳት ፕሮፌሰሮችና ከዚያ በላይ ማዕረግ ያላቸው ኢትዮጵያዊ መምህራን፣ ትምህርታቸውን ጨርሰው ከሚመጡ 470 ምሁራንና አሁን በማተማር ላይ ካሉ 180 የውጭ አገር ምሁራን ጋር ተዳምሮ ከ1000 በላይ ረዳት ፕሮፌሰርና ከዚያ በላይ ማዕረግ ያላቸው ምሁራኖች ችግር ፈቺ ምርምር የማካሄድና ድህረ ምረቃ ተማሪዎችን የማማከር አቅማችን በእጥፍ እያደገ ነው /ሰንጠረዥ 3 እና 5 ይመልከቱ/

**የመረጃ ክምችት ማዘመንና ማሳደግ**

- በሩብ ዓመቱ እንዲታተሙ ከታቀዱ 100 ጆርናሎች 92 የታተሙ ሲሆን ከእነዚህም 88 በውጭ ሀገር ጆርናሎችና 4 በሀገር ውስጥ ጆርናሎች የታተሙ ናቸው
- የዲጂታል ዳታ ሪፖዚቶሪ ፖሊሲ ሴኔት አቅርቦ ማጸደቅ ፖሊሲ ተረቆ ለውይይት ተዘጋጅቷል

**የተገኙ ግኑኝነቶች/ፕሮጄክቶች ብዛት**

- በህግና ገቨርናንስ ኮሌጅ ከ4 ተቋማት ጋር በምርምርና ድ/ምረቃ ትምህርት ዘርፍ ግንኙነቶችን ለመመስረት ዝግጅት ተጀምሯል፣ ከሚመለከታቸው ጋር ለመወያየት ቅድመ ዝግጅት ማድረግ፣ የግንኙነት መስኮችን መለየትና ማኑዋሎችን ማዘጋጀት በሂደት ላይ ይገኛል
- መምህራን የምርምር ፕሮጀክቶች ፕሮፖዛሎችን እንዲያስገቡ ጥሪ ቢደረግም በክረምት መርሃ- ግብር ካለው ሥራ መደራረብና የዩኒቨርስቲው ስልጠና የተነሣ በተቀመጠው የግዜ ሰሌዳ ማስገባት አልተቻለም። ስለዚህም ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጣቸው ተደርጓል
- ከ 2007 የበጀት ዓመት ጀምሮ በሂደት ላይ ያሉ 25 ፕሮጀክቶች እንዲጠናቀቁ ጥረት እየተደረገ ነው
- በምርምር ክህሎትየአቅም ግንባታ ስልጠናዎች እየተሰጡ ነው

**ዕውቅና ለመስጠትና ለምርምር የሚውል የገንዘብ ምንጭ ማፈላለግ**

- 6 የምርምርና ማማከር ግራንት ጥሪዎች ለኮሌጆችና ኢንስቲትዩቶች ተልኮ የተዘጋጁ concept note ለፋይናንስ ምንጮች ተልኳል፡ ከእነዚህም መካከል
- Eco-ORBIT (Trans-boundary river basin management in Omo-Gibe basin with implication for Lake Turkana
- Enhancing Socio-Ecological Resilience to Climate Change
- Waste recycling and bio-energy Concept notes developed and submitted
- Trans-boundary Cooperation for Omo-Gibe River Basin Integrated with Turkana for Climate-Resilient Green Economic Growth
- Strengthening engineering education through UIL for improved innovation and employability of graduates የሚሉት ይገኙበታል

**ዓላማ 3.2. ፈጠራና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማስፋፋት**

**የቴክኖሎጂ ፈጠራና ሽግግርና አህዝቦት**

- በአለም ጤና ጥበቃና አለማቀፍ ደረጃዎች ድርጅት ISO/IEC 17025 መመሪያ መሠረት የመድኃኒት ጥራትና ምርምር ማዕከሉና ጥራት ሲሰተም ተመስርቷል፤ የአለማቀፍ ደረጃዎች ድርጅትና የአለም ጤና ጥበቃ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እየተጠበቀ ነው
- በ Medication Registration Dossier evaluation ለ150 መርማሪዎች ስልጠና ተሰጥቷል
- በ Quality system and GLP\GMP training ለ40 ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል
- የህክምና ምዝገባ የሰውና እንስሳት መድኃኒት ጥናትና ጥራት ቁጥጥር፣ ፋርማሲዩቲካል፣ ባዮቴክኖሎጂካልና ተጓዳኝ መድኃኒቶች ጥናት ላቦራቶር ተመስርቷል

## ፕሮግራም 4. ማህበረሰብ አገልግሎትና አሳታፊነት ልዕቀት

የመማር/ ማስተማር፣ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ጥረቶች የአካባቢውን ማህበረሰብ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የባለድርሻ አካላት የተቀናጀ ጥረት ይፈልጋል። የዩኒቨርሲቲውም የማህበረሰብ አቀፍ የትምህርት ፍልስፍናም ከማህበረሰቡ ጋር እየተካሄደ ያለውን የሁለትዮሽ ጥምርታ ዕውን እንዲያደርግና የንድፈ-ሃሳብ ትምህርት ከህብረተሰቡ የዕለት ተዕለት ህይወት ጋር ማስተሳሰርን ይሻል። ይህን መሰረት በማድረግ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል። አዲስ የተገነባው ሆስፒታል የጤና ዘርፍ መማር/ ማስተማር ሂደትን ለማሻሻልና የምርምር ጥረቶቻችን እንዲሳኩ የሚከተሉት ተግባራትን አከናውኗል። ይህ ፕሮግራም ዩኒቨርሲቲዉ ከሚያስፈፅማቸዉ ዋና ዋና አላማዎች አንዱ ሲሆን ይህ ፕሮግራም በአብዛኛዉ ከማህበረሰቡ ጋር በቀጥታ ለማገናኘት እንደ ድልድይ ያገለግላል። ዩኒቨርሲቲያችንም ይህንኑ በመገንዘብ ለዚሁ ስራ ያሞች ዘንድ የራሱን የማህበረሰብ አቀፍ የትምህርት ፍልስፍና ቀርፆ ማህበረሰቡ መሃል በመግባት የማህበረሰቡን ችግር ሲፈታ ቆይቷል። በመሆኑም በዚህ በዝግጅት ምዕራፍም ከዚሁ ከማህበረሰብ አገልግሎት ጋር ተያይዞ የተሰሩ ስራዎችን በዝርዝር ይቀርባል

### ዓላማ 4.1. በማህበረሰብ አቀፍ ትምህርት የማህበረሰቡን አገልግሎት ማጠናከር

**ሠንጠረዥ 16 ማህበረሰብ አገልግሎት**

| ቁልፍ የአፈፃፀም ማሳያዎች | መለኪያ | የዓመቱ ዕቅድ | የ1ኛ ሩብ ዓመት | | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | |
| **1. በዩኒቨርሲቲው ሆስፒታል የተገለገሉ ደንበኞች** | ተጠቃሚ ቁጥር | | | | |
| - ድንገተኛ ክፍል ታካሚዎች | ተጠቃሚ ቁጥር | 20,000 | 5000 | 4227 | 85 |
| - ተኝተው የታከሙ Admissions | ተጠቃሚ ቁጥር | 20,000 | 5000 | 4686 | 94 |
| - ተመላላሽ ታካሚዎች | ተጠቃሚ ቁጥር | 300,000 | 75000 | 50829 | 68 |
| - የማዋለድ ህክምና ተጠቃሚ ቁጥር | ተጠቃሚ ቁጥር | 6000 | 1500 | 1169 | 78 |
| አይን ህክምና ተጠቃሚዎች ቁጥር | ተጠቃሚ ቁጥር | 47750 | 12038 | 32842 | 273 |
| - በሆስፒታል | ተጠቃሚ ቁጥር | 24550 | 6138 | 6342 | 103 |
| - በተመላላሽ | ተጠቃሚ ቁጥር | 23200 | 5900 | 26500 | 449 |
| ከባድ ቀዶ ጥገና አገልግሎት | ተጠቃሚ ቁጥር | ND | ND | 938 | ND |
| አልትራሳውንድ | ተጠቃሚ ቁጥር | 3500 | 875 | 997 | 114 |
| ኮንቬንሽናል ራዲዮግራፊ | ተጠቃሚ ቁጥር | 17 | 4250 | 3839 | 90 |
| Prosthesi, Orthosis, Walking Aids, ተጠቃሚዎች | ተጠቃሚ ቁጥር | 1600 | 418 | 418 | 100 |
| ART የተሰጣቸው HIV +ve ነፍሰጡርና የሚያጠቡ እናቶች | ተጠቃሚ ቁጥር | 50 | 12 | 3 | 25 |
| ከደም ባንክ የተጠቀመ ደም መጠን | ዩኒት | 100 | 100 | 746 | 746 |
| **ንዑስ ድምር** | | **445,167** | **110,813** | **133,536** | 121 |
| በ DTTP ተደራሽ የሆኑ ማህበረሰብ | ተጠቃሚ ቁጥር | 13177 | 8243 | 8407 | 102 |
| ግብርና ቴክኖሎጂዎችን ለማህበረሰቡ በማዳረስ | ተጠቃሚ ቁጥር | 2000 | 1834 | 1834 | 100 |
| የባለድርሻ የምክክር መድረኮች | ተጠቃሚ ቁጥር | 2 | 2 | 2 | 100 |
| የኮሌጅ-ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ት ቤት ግኑኝነት | ተጠቃሚ ቁጥር | 3 | 1 | 100 | 10000 |
| ከተቋማት ጋር በቅንጅት የተከናወኑ ማህበረሰብ አገልግሎት | ተጠቃሚ ቁጥር | 1 | 11 | 10 | 91 |
| የ DTTP እና CBTP ተሞክሮዎችን ለመቀሌ፣ ጎንደርና ደብረታቦር ዩኒቨረሲቲዎች አካፍለናል | ተጠቃሚ ቁጥር | 24 | 24 | 24 | 100 |
| በነፃ የህግ አገልግሎት የተገለገሉ ደንበኞች | ተጠቃሚ ቁጥር | 10000 | 523 | 523 | 100 |
| **ለት/ቤቶችና ሌሎች መ/ቤቶች የተደረገ ድጋፍ** | **ዓይነት/ ብር** | **284,346** | **284,346** | **284,346** | **100** |
| **ጠቅላላ የማህበረሰብ አገልግሎት ድምር በዓይነት** | **ተጠቃሚ ቁጥር** | **458,436** | **232,265** | **273,746** | **105** |

**በማህበረሰብ አገልግሎት የተሰሩ ስራዎች**

- 273,746 የማህበረሰቡ አካላት በነፃ የህግ አገልግሎት፣ በ CBTP እና DTTP፣ ልምድ ልውውጥ በማድረግ፣ በባለድርሻ የምክክር መድረኮችና ከተቋማት ጋር በቅንጅት በተከናወኑ ስራዎች ተጠቃሚ ሆነዋል። ይህ አፈፃፀም በዕቅድ ከያዝነው በላይ 104 በመቶ አፈፃፀም በማሳየት የተሻለ ስራ መሰራቱን ያሳያል።
- ከዚህ በተጨማሪ ግምቱ 284,346 ብር የሚያወጣ ድጋፍ በዓይነት ለማህበረሰቡ ተሰጥቷል።
- በዘመናዊ ሁነኔታ የተደራጀው የጅማ ዩኒቨርሲቲ የህክምና ማዕከል ከዚህ በፊት በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የማይሰጡ አዳዲስ የጤና ህክምና አገልግሎቶች ለምሳሌ ያህል /የህፃናት ካንሰር ህክምና፣ የኩላሊት ዕጥበት፣ እጅግ ዘመናዊ የስነምግብ ህክምና/ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል። በተጨማሪም በዚህ ሩብ ዓመት ለ133,536 የማህበረሰቡ አካላት የህክምና አገልግሎት በመስጠት ከዕቅዱ በላይ የ121 ከመቶ አፈፃፀም አሳይቷል። በዚህም ለድንገተኛ ተኝቶ የመታከም፣ የተመላላሽ ህክምና፣ የማዋለድ አገልግሎት፣ የአይን ህክምና፣ የከባድ ቀዶ ጥገና አገልግሎት፣ አልትራሳውንድ፣ ኮንቬንሽናል ራዲዮግራፊ፣ Prosthesi, Orthosis, Walking AIDS፣ በART የHIV Positive ነፍሰጡርና የሚያጠቡ እናቶች አገልግሎት ተሰጥቷል
- ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ለመጡ 196 ህሙማን መድሃኒት የተላመደ ቲቢ ምርመራና ህክምና ክትትል ተደርጓል፣ ለሸነን ጊቤ፣ ለመቱ፣ ነቀምቴ፣ ለጊምቢ፣ ለነጆና ደምቢዶሎ ሆስፒታሎች MDR-TB ዲያግኖሲስ፣ ህክምና ክትትልና ፊፈራል አገልግሎት ተሰጥቷል
- በነፃ የህግ አገልግሎት ዘርፍ ከዚህ በፊት በተለያዩ ወረዳዎችና ጅማ ከተማ ከነበሩ 9 የህግ አገልግሎት መስጫ ማዕከላቶች በተጨማሪ በጅማ ማረሚያ ቤት Comprehensive Legal Clinic ተከፍቷል። ይህም ታራሚዎች ስለመብታቸዉና ሰለተከሰሱበት ወንጀል መረጃና የሕግ ምክር የሚያገኙበት ሲሆን በተጨማሪም (እንደ ቴክኖሎጂ ሽግግር) ታራሚዎች ጅማ ከተማ ላይ /ማረሚያ ቤቱ ዉስጥ ሆነው በፕላዝማ ነቀምቴና አዳማ ላይ ባሉ ሰበር ችሎትና ተዘዋዋሪ ችሎቶች ላይ የሚደረጉ የፍርድ ሂደታቸዉን መከታተል ይችላሉ።

  በተጨማሪም የነፃ የህግ አገልግሎት ማዕከል ከሚከተሉት ተቋማት ጋር በቅንጅት በመስራት ላይ ይገኛል።

  - ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት
  - የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን
  - ጅማ ዞን ማራሚያ ቤት አስተዳደር
  - ከሰባት የወረዳ ፍ/ቤቶች (ጅማ ወረዳ፤ ሸቤ፤ጎማ፤ጌራ፤ኦሞ ናዳ፤ዴዶ እና ቀርሳ ወረዳ)
  - ከጅማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት
  - ከ አራት የወረዳ ሴቶች እና ህፃናት ጽ/ቤት ጋር
  - ከሶስት የፖሊስ መምሪያ ጋር
  - ከ ሶስት የወረዳ ሠራተኛ እና ማህበራዊ ጽ/ቤት
  - ከጅማ ዞን አቃብ ህግ ጽ/ቤት
  - በጅማ ከተማ አገልግሎት የህፃናት ፓርላማ ለማቋቋኽ የሚያስፈልጉ ነገሮች በማሟላት አገልግሎት እንዲጀምር ተደርጓል።
  - የሕዝብ የህግ ትምህርት (Public legal education) ማዕከላት በጅማ ከተማ መናኸርያና ጅማ ማረሚያ ቤት ቅጥር ግቢዎች ውስጥ ተቋቁሟል።

**ከባለድርሻዎች ጋር በትብብር የተሰሩ ስራዎች**

- ጅማ ስማርት ከተማ በሚል ስያሜ የጅማ ከተማን አይሲቲ አገልግሎት ለማሻሻል ፕሮጄክት ተጀምሯል
- የግብርና ባዮቴክኖሎጂ የምዕራብ ዘርፍ የመጀመሪያ ዙር ዓውደጥናት ተካሂዷል
- ከ GKEN ጋር በመተባበር design and analysis of experiments and analysis of experiments and publication of peer reviewed journals የአጭር ጊዜ ስልጠና ተሰጥል
- ከሉሊ ኮንሰልተንሲ ጋር በመተባበር የኢትዮጵያ የመንገድ ደህንነት ጉባዔ በአዲስ አበባ ተካሂዷል
- መቀመጫውን አሜሪካ ካደረገው አስላን ፕሮጄክት ጋር በመተባበር የህፃናት ካንሰር ማዕከል ስራ ተጀምሯል
- የማይክሮባዮሎጂ ትምህርት ክፍል ከቻይና የሳይንስ አካዳሚ ጋር የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርሟል

- በ DTTPና CBTP ልምዶችን ለመቀሌ፣ ደብረታቦርና ጎንደር ዩኒቨርሲቲዎች አካፍለናል
- ለምርምር ረዳቶችና ለተመራማሪዎች ስለኤሌክትሮኒክ መረጃ አሰባሰብ ሥልጠና ተሰጥቷል
- የምርምር ፅሁፎች ለህትመት ለጆርናሎች ተልኳል
- ለ11 የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲና 3 የ TVET ኮሌጅ መምህራን ለአራት ቀናት በ Grant Project Writing፣ Grant Project Management፡ Scientific Writing፡ Publication in Peer-Reviewed Journal እና Ethics in Research and Publication ስልጠና ተሰጥቷል
- ለአርሲ ዩኒቨርሲቲ ስለ ምርምርና ድህርምረቃ ፕሮግራሞች ላይ የልምድ ልውውጥ ተሰጥቷል ፡፡

## የጅማ ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ ተኮር ራዲዮ ጣቢያ

- ጣቢያው በተለያዩ ምክንያቶች የተደራሽነትና ተደማጭነት ችግር ገጥሞት ነበር ፡፡ በቅርቡ በቦርድ አመራሩና ሰራተኞች በተወሰዱ ማሻሻያዎች ጣቢያው የተሻሉ ለውጦችን ማስመዝገብ ተችሏል፡፡
- ለአንድ አመት ተኩል በጥራት ወደ አድማጩ ፕሮግራሞቹን ማድረስ ያስቸገረውን የቴክኒክ ችግር ለመቅረፍ የተለያዩ የሚዲያ ተቋማት ድጋፍ ተጠይቆ ሊሳካ ባይችልም ጣቢያው ችግሩን በራሱ ለመቅረፍ ሞክሮ ተሳክቶለታል
- በአሁኑ ሰዓት ራዲዮ ጣቢያው በጅማ ከተማ፣ በጅማ ዞን 14 ወረዳዎች፣ በቡኖ በደሌ 3 ወረዳዎች ላይ ሙሉ በሙሉ የሚደመጥ ሲሆን በጅማ ዞን 7 ወረዳዎች፣ የም ልዩ ወረዳ፣ ዳውሮ ዞን፣ ሀዲያ ሆሳህና፣ ጉራጌና ጅማ አርጆ አካባቢ በከፊል ይደመጣል
- ጣቢያውን ይበልጥ ተደራሽ ለማድረግ የዕቃ ግዥ በሂደት ይገኛል፤ ዘመናዊና ደረጃውን የጠበቀ ስቱዲዮ ግንባታም እየተከናወነ ነው፡፡
- ለራዲዮ ጣቢያው የተፈቀዱ የስራ መደቦች ላይ 4 ሰራተኞች ቅጥር ተፈፅሟል፣
- ስራ አቁመው የነበሩ የራዲዮ ጣቢያው በጎፈቃደኞች ዳግም ጥሪ ተደርጎላቸው ስራ ላይ ይገኛሉ፣ በራዲዮ ጣቢያው ውስጥ ከሚገኙ ሰራተኞች ጋር ተከታታይ የሆነ ምክክር ተደርጎ የነበሩ ችግሮችን በውይይጥ ለመቅረፍ ተችሏል
- የሰራተኞችና የበጎ ፈቃደኞች የስራ ዝርዝርና ድልደላ ተደርጓል፣ በዚህ መረሃግብር መሰረት ወደ ስራ ተገብቶአል
- የአካባቢውን ማህበረሰብ ማዕከል ባደረገ መልኩ በአማርኛና አፋን ኦሮሞ ቋንቋ ፕሮግራሞች አየር ላይ ውሏል
- በቀጣይ ለራዲዮ ጣቢያ የሚያስፈልጉ የስራ መደቦችና የቁሳቁስ ግዥበሂደት ላይ ይገኛል
- የጣቢያውን የስራ ሂደት በህግና በደምብ ለመምራት ያስችል ዘንድ የጣቢያው የስቱዲዮ ፓሊሲ እየተዘጋጀ ነው

## ዓላማ 4.2. ዘመናዊ/ New age/ የህክምና ማዕከል መገንባት

**ሠንጠረዥ 17** የዩኒቨርሲቲው ህክምና ማዕከል

| ቁልፍ የአፈፃፀም ማሳያዎች | መለኪያ | የዓመቱ ዕቅድ | የ1ኛ ሩብ ዓመት | | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | |
| የአዲሱን ሆስፒታል ኔትወርክ ኮንፊገሬሽን ማጠናቀቀ | መቶኛ | 100 | 10 | 10 | 100 |
| የማዕከሉን ዳታ ሴንተር ዲዛይን እንደገና መስራት | መቶኛ | 100 | 0 | 0 | 0 |
| በቴክኖሎጂ (ICT) አጠቃቀም ላይ የሠለጠኑ ሠራተኞች | ቁጥር | 50 | 0 | 0 | 0 |
| ሕክምና ያገኙ ሠራተኞች ብዛት | ቁጥር | 150 | 20 | 8 | 40 |
| በሆስፒታል የኢንተርኔት ኔትወርክ ተደራሽነት | ተጠቃሚ ቁጥር | 1000 | 250 | 220 | 88 |
| ሃርድዌርና ሶፍትዌር ጥገና ያገኙ | ቁጥር | 1000 | 250 | 300 | 120 |
| ሶፍትዌር በኮምፒውተሮች መጫንና ማከፈፋል | ቁጥር | 400 | 200 | 250 | 125 |
| የሜዲካል ማዕከሉን ሰርቨር configuring ማድረግ | ቁጥር | ND | ND | 30 | ND |
| የፋይበር ኦፒተክስ ኬብል መዘርጋት | ቁጥር | ND | 10 | 10 | 100 |
| ኔትወርክ አድሚንስትሬሽን ስልጠና | ቁጥር | ND | ND | 10 | ND |
| ኮምፒውተር ላቦራቶር ማቋቋም | ቁጥር | 2 | 2 | - | 0 |
| ለአዲሱ ሆስፒታል ኬብል እንዳይጎዳ መሸፈን | ቁጥር | ND | 400 | 2 | 1 |
| አዲስ የተሰራውን ሶፍትዌር በየክፍሉ ስራ ማስጀመር | ቁጥር | 3 | 1 | 4 | 400 |
| ለአዲሱ ሆስፒታል open clinic software መጀመር | ቁጥር | 1 | 1 | 1 | 100 |
| ዋየለርለስ አክሰስ ፖይንት መግጠም | ቁጥር | ND | 1 | 1 | 100 |
| ታካሚዎች አገልግሎት ለማግኘት የሚቆዩበት ሰዓት በደቂቃ (በየሩብ ዓመት በሆስፒታሉ በሚከናወን ዳሰሳ ጥናት መሰረት) | ደቂቃ | 30 ደቂቃ | 45 ደቂቃ | 86 ደቂቃ | 49 |
| በሆስፒታሉ የተሰበሰበ ገቢ | ብር ሚሊዮን | 18 | 3 | 2.8 | 93.3 |
| Patient day equivalents per doctor | | | | 1269 | |
| በቀዶጠጋኝ ሐኪም የተሰራ ዋና ቀዶ ጥገና በሃኪም | ቁጥር | 300 | 500 | 529 | 106 |
| ስልጠና መስጠት | ቁጥር | 150 | 48 | 8 | 17 |
| የህክምና መሳሪያዎች ጥገና | ቁጥር | 100 | 88 | 88 | 100 |
| ባዮሜዲካል ኢንጅነሪንግ ባለሙያዎች ስልጠና | ቁጥር | 8 | 8 | 50 | 625 |
| የውስጥ ገቢ አጠቃቀም | በመቶኛ | 100 | 25 | 0 | 0 |
| የሆስፒታሎች ተቋማዊ ለውጥ ደረጃን ከማሟላት አንፃር | በመቶኛ | 90 | 90 | 0 | 0 |

## ዓላማ 4.3. ዘለቄታዊ የአካባቢ ጥበቃን ማሳደግ

- የአየር ንብረት ለውጥን ለመላመድና ለማገገም የሚረዱ ቴክኖሎጂዎችን ለማፍለቅ ይረዳ ዘንድ ሶስት የተመረጡ ስንዴና አኩሪ አተር፣ አንድ ድንች፣ 7 የበቆሎ ዝርያዎች ሙከራና ማረጋገጫ ጥናት ተከናውኖ ቴክኖሎጂ የማሸጋገር ስራ ተከናውኗል፣ 27764 ገበሬዎች ተጠቃሚ ሆነዋል
- የአፈር መከላትን ለመከላከል ህብረተሰቡን ያሳተፈ የ6 ኪሜ የአገር በቀል ችግኝ ተከላ ተደርጓል፣ የፓፓያ ዝርያ ማላመድና የበቄላ ዝርያ ጥናት ተካሂዷል፣ ገበሬዎች ተጠቃሚ ሆነዋል
- የጓሮ አትክትልና ፍራፍሬ የስነምግብ ትምህርትና ስልጠና ለ2500 ገበሬዎች ተሰጥቷል
- በአካባቢ ከሚገኙ ቁሳቁሶች የተሰራ አትክልትና ፍራፍሬ ማቆያ ለተደራጁ የአትክልትና ፍራፍሬ መሸጫ ሱቆች ተሰርቷል፣ በጨፌ መሬት ጥቅምና እንክብካቤ ላይ በማይክሮ ለተደራጁ ወጣቶች ስልጠና ተሠጥቷል፡፡

## የዓለማቀፋዊነትና ተቋማዊ ትብብር ትኩረት መስክ

ጠንካራ ውድድርና የስራ ዕድል ባለበት ዓለማቀፋዊ ነባራዊ ሁኔታ በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ አሸናፊ ሆኖ ለመዝለቅ ተማሪዎችና መምህራን በዘርፉ በቂና ተመጣጣኝ ዕውቀትና ክህሎት ሊኖራቸው ይገባል። ስለሆነም የምንሰጠው ትምህርት ምሩቃንን በብሔራዊና ዓለማቀፍ ደረጃ ብቁና ተወዳዳሪ እንዲያደርጋቸው ከሚቀያየረው ዓለማቀፋዊ ሁነት ጋር መላመድና ተወደዳዳሪ ሆኖ ለመዝለቅ ጥረት እየተደረገ ነው። ለዚህም መምህራንና ተማሪዎችን ማብቃት የሚያስችል የልምድ ልውውጥ፣ የጋራ ህትመትና ለምርምር የሚውል ገንዘብ ለማፈላለግ የሚከተሉት ስራዎች ተከናውነዋል።

### ዓላማ 5.1. ዓለማቀፋዊ ተወዳዳሪ ትምህርትና የምርምር መስኮችን ማበልፀግ

**ሠንጠረዥ 18** ዓለማቀፋዊ የምርምር መስኮች

| ቁልፍ የአፈፃጸም አመለካከት ወይም ማሳየዎች | መለኪያ | ዕቅድ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | የዓመት ዕቅድ | አንደኛ ሩብ ዓምት | | |
| | | | ዕቅድ | ክንውን | % |
| ዓለማቀፋዊ ቅቡልነት ያላቸው ስርዓተ ትምህርት | ቁጥር | 2 | 2 | 2 | 100 |
| በ ISO 9000 ዕውቅና ያገኙ ፕሮግራሞች (ስምንቱ ISO 9000 የትምህርት ጥራት አስተዳደር፣ ተማሪ ተኮር ተቋም፣ የአመራር ጥራት፣ ማህበረሰቡ ተሳትፎ፣ አመራር አቀራረብ፣. አሰራር ሂደት፣ ዘላቂ ለውጥ፣ የጋራ ተጠቃሚነት መሰረት ያደረገ የባለድርሻ ግኑኝነት) | ቁጥር | 8 | 2 | 0 | 0 |
| የተሰጡ አጫጭር ዓለማቀፋዊ ኮርሶች | ቁጥር | 14 | 2 | 0 | 0 |
| ለዓለማቀፍ ፕሮግራም የተደራጁ አብያተ መፃህፍት | ቁጥር | 1 | 0 | 00 | |

### ዓላማ 5.2. ዓለማቀፍ ደረጃ የሚያሟሉ መምህራንና ተማሪዎችን መሳብና ስራ ላይ ማቆየት

**ሠንጠረዥ 19 በምርምርና በትምህርት ዓለማቀፋዊ ትብብርን ለመመስረት/ ለማጠናከር የተከናወኑ ስራዎች**

| ቁልፍ የአፈፃፀም ማሳያዎች | መለኪያ | የዓመቱ ዕቅድ | የ1ኛ ሩብ ዓመት | | አፈፃፀም በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዕቅድ | ክንውን | |
| ዓለማቀፍ ተቋማዊ ትብብር ማስተባበሪያ ቢሮ እንደገና ማዋቀር | ቁጥር | 1 | 0 | 0 | 0 |
| በካምፓሶች አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር የተደራጁ ፋሲሊቲዎች | ቁጥር | 4 | 0 | 0 | 0 |
| ከዕውቅ ዓለማቀፍ ተቋማት ጋር የተመሰረቱ ትብብሮች | ቁጥር | 10 | 4 | 4 | 100 |
| የተከናወነ የተማሪዎች ልውውጥ | | 5 | 4 | 4 | 100 |
| የተከናወነ የመምህራን ልውውጥ | ቁጥር | 2 | 1 | 1 | 100 |
| የተዘጋጁ ዓለማቀፍ ስምምነትና ትብብር መመሪያ/ ፕሮቶኮል | ቁጥር | 4 | 0 | 0 | 0 |
| የዶክቶራል ስልጠና መመሪያውን ማስፀደቀቅና ማሳተም | ቁጥር | 1 | 0 | 0 | 0 |
| በዓለማቀፍ ፕሮግራም የተመዘገቡ ተማሪዎች /አዲስ-አበባና ሶማሊላንድ (Lucy 3, ABH 2, Hargeisa 2) | ካምፓስ ቁጥር | 7 | 7 | 4 | 57 |

## ዓላማ 5.3. በምርምርና በትምህርት ዓለማቀፋዊ ትብብርን መመስረት/ ማጠናከር

**ሠንጠረዥ 20** ፕሮጄክቶችና የምርምር ማዕከላትና ኢንስቲትዩቶች ውጤቶች

| በኢንስቲትዩቱ/ምርምር ማዕከላቱ የተከናወኑ ስራዎች | ምርምር ማዕከል | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ማይክ-ባቱረዮሎጂ | ባዮቴክኖሎጂ | መድኃኒት ጥራት | ትሮፒካል ተላላፊ በሽታዎች | ግልገል ጊቤ | ሞሎኪውላር ባዮሎጂ | ድምር |
| በፕሮጀክቱ የተሰሩ የምርምር ስራዎች | | 2 | 6 | 6 | 2 | 2 | 18 |
| በፕሮጀክቱ አገልግሎት ያገኙ ማህበረሰብ ክፍል | 2 | 150 | 40 | 4 | 2 | 2 | 200 |
| በፕሮጀክቱ ትምህርት ዕድል ያገኙ/ ያጠናቀቁ መምህራን | 2 | 3 | 5 | 6 | - | 2 | 18 |
| የሶስተኛ ዲግሪ | | 4 | 4 | 6 | | 125 | 139 |
| የሁለተኛ ዲግሪ | | 0 | 1 | 2 | 34 | 3 | 40 |
| የተሰጡ አጫጭር ስልጠናዎች | 3 | 0 | 8 | 2 | 15 | 2 | 30 |
| በ Research Grant የተገኘ ገንዘብ | | 20 ሚሊዮን | 2.8 ሚሊዮን | 2 ሚሊዮን | | 1 | 24.8 ሚሊዮን |
| ከግራንት በተገኘው ድጋፍ የመምህራን ተሳትፎ | | 4 | 10 | 3 | 3 | - | 20 |
| የምርምር ፕሮጀክቶች ያሉበት ሁኔታ | | | | | | 2 | 2 |
| አዲስ የተጀመረ የምርምር ፕሮጀክት | | | 8 | 1 | | | 9 |
| በሂደት ላይ ያለ የምርምር ፕሮ ጀክት | | | 12 | 6 | | 3 | 21 |
| በ2009 ዓ.ም የተቋረጠ የምርምር ፕሮጀክት | | | 0 | 0 | | | - |
| የተጠናቀቀ የምርምር ፕሮጀክት | 1 | | | 1 | | 1 | 3 |
| በጫጋ የምርምር ፕሮጀክት የተሳተፉ ድህረምረቃ ተማሪዎች | 1 | | 10 | 6 | | 1 | 18 |
| በታወቁ ዓለም አቀፍ ምርምር ጆርናሎች የታተሙ | 0 | | 12 | 4 | | - | 16 |
| በሀገር ውስጥ ጆርናል የታተመ ምርምር ስራ | 1 | | 12 | 1 | | 1 | 15 |
| በጥናትና ምርምር ስራ የተሳተፉ መምህራን | | | 10 | 3 | | 1 | 14 |
| ወርክ ሾፕ (Work Shop on Pharmaceutical Science) | 1 | | 1 | 1 | | 2 | 5 |
| - Scientific Seminars | | | 2 | 1 | | - | 3 |
| - In- Service training | 5 | | 2 | | | 3 | 10 |
| ምርምር ውጤቶችን በታወቀ ጆርናል ማሳተም | 1 | | 4 | | | 1 | 6 |

- በግልገል ጊቤ የመስክ ምርምር ማዕከል ከተሰበሰቡና በተቀናጁ የሰርቬላንስ መረጃዎች የ2600 በቤተሰብ ደረጃ መረጃ የማመሳከር ስራ ተሰርቷል፣
- 2695 መረጃዎችን ወደ ዳታቤዝ ለማስገባትና ለማፅዳት ታቅዶ 4186 ተሰርቷል፤ ይህም አፈፃፀም 155 በመቶ ሆኗል። ይህ ልዩነት የተከሰተው ከባለፈው ሩብ ዓመት የቀሩት በመጠናቀቃቸው የመጣ ልዩነት ነው
- Anti-malarial bio-functionality evaluation of endemic plants of Ethiopia የሚል በVLIR-JU ከሚታገዝ ፕሮጄክት 6 ጆርናሎች ታትመዋል
- Development of in-vivo relevant dissolution systems for neglected tropical medicines የሚለው በ BOF-Ghent University ከሚታገዘው ፕሮጄክት 4 ጆርናሎች ታትመዋል፣ ሁለት ቴክኖሎጂዎች ተሸጋግረዋል

- Development and evolution of N-alkylamides from endemic plants of Ethiopia for treatment of infectious diseases የሚለው በVLIR-JU ከሚታገዘው ፕሮጄክት 1 ጆርናል ታትሟል
- Pharmaceutical Exciepent and drug development from Boswelic species indigenous to Ethiopia የሚለውና Anti –quorum sensing potential of peptides from endemic natural and other sources in Ethiopia: the solution to antimicrobial resistance የሚለው በጅማ ዩኒቨርሲቲ የሚታገዘው ፕሮጄክት የምርምር ውጤቶች ለህትመት ተልከዋል
- Quality of selected medicines in Ethiopia የሚለው በVLIR-JU የሚታገዘው ፕሮጄክት 12 የምርምር ውጤቶች ታትመዋል፣ ሁለት ቴክኖሎጂዎች ለተጠቃሚዎች ተሸጋግረዋል
- Mobile health (mheath) based intervention in supporting adherence to antiretroviral therapy retention in care among pregnant women living with human immunodeficiency virus የሚለው ፕሮጄክት ለህትመት ተልኳል
- በአለም ጤና ጥበቃና ISO/IEC 17025 መመሪያ መሠረት የምርምር ማዕከሉ ጥራት ሲሰተም ተመስርቷል፣ ለመድኃኒት ጥናትና ጥራት ቁጥጥር፣ ፋርማሲዩቲካል፣ ባዮቴክኖሎጂካልና ተጓዳኝ መድኃኒቶች ጥናት ላቦራቶር ተመስርቷል
- ለድህረና ቅድመምረቃ ተማሪዎች ተግባራዊ ስልጠና ድጋፍ ተደርጓል ፣ ለአዳዲስ መድኃኒቶችና መድሃኒት አሰጣጥ ሲስተም የቅድመና ድህረ ክሊኒካል ምስረታ ድጋፍ ተደርጓል
-

## ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች

### ያጋጠሙ ችግሮች

- በመንግስት የተመደቡ የክረምት ተማሪዎች ዝርዝር በወቅቱ አለመድረሱ ምዝገባና የትምህርት ጊዜ መዘግየት
- በአንዳንድ ትምህርት መስኮች የሁለተኛና ሶስተኛ ዲግሪ ያላቸው መምህራን ከገበያ አለመገኘት
- የመማሪያ ክፍል በቂ ያለመሆን
- የማዕቀፍ ግዥ ከመጓተቱ በተጨማሪ የሚቀርቡ ዕቃዎች የጥራት ማነስና ተለዋዋጭ ዕቃ ማጣታቸዉ
- ሹፌሮች ለስራ አዲስ አበባ ሲመላለሱ የመኪና ማቆሚያ ያለመኖርና የሹፌሮች ደመወዝ ዝቅተኛ መሆን
- የውሃና መብራት መቆራረጥና እጥረት
- የግንባታዎች በተቋራጮች አቅም ማነስና ሌሎች ምክንያቶች ግንባታዎች ቶሎ ተጠናቆ ለአገልግሎት አለመዋሉ
- በደመወዝ ምክንያት የአስተዳደር ሠራተኞች ስራ ለቆ መሄድ በስራችን ከፍተኛ የሆነ ችግር ፈጥረዋል፡፡

### የተሰጡ መፍትሄዎች

- የክረምት ተማሪዎች ዝርዝር በወቅቱ እንዲላክልን ጠይቀናል
- ከህንድ ሀገር ለመቅጠር ጥረት እየተደረገ ነው
- በእጃችን ያለውን ሪሶርስ በፈረቃ፣ በቁጠባና በአግባቡ እየተጠቀምን ነው
- ግዥ በወቅቱ እንዲከናወን ጥብቅ ክትትልና ድጋፍ እያደረግን ነው
- ጥብቅ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ችግሮቹን ለመፍታት ቢቻልም አንዳንድ ችግሮች ግን እየቀጠሉ ይገኛሉ